


በጎጃም ሀ/ስብከት አዴት የደብረ ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን

# ትንሣኤ



በሸዋ ሀ/ስብከት በሰላሌ አውራጃ ፍቼ የሚገኘው ሽንኩርት ·የደብረ ፍሥሐ ቅ· ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፲፯፫ የመጋቢትና የሚያዝያ ወራት ፲፱፻፹፬ ዓ·ም·

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም/ አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

## ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእሰ አንቀጽ (ጾም ለሰላም) | ፪ |
| ዜና ዕረፍት (የመሪጌታ ፍሥሐ ባንቴ) | ፬ |
| ሆሣዕና (ሰላምሽ ዛሬ ነበር) | ፬ |
| ጸሎተ ሐሙስ የቀን ቅዱስ | ፯ |
| ዲያብሎስ ታሠረ | ፯ |
| የሰላም አዳራሽ | ፰ |
| ተጠበቁ አትደንግጡ | ፱ |
| ዜና ሊቃውንት | ፲፩ |
| በተመረጠች ቀን እሰማሃለሁ | ፲፫ |
| የርእሰ ደብር አበበ ጅሩ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ | ፲፬ |
| ሁሉ ተፈጸመ አለ | ፲፭ |
| የሴቶች ዓምድ/ሴቶች ትንሣኤውን ሰበኩ | ፲፮ |
| የመልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው አጭር የሕይወት ታሪክ | ፲፰ |
| ከቅዱስ መጽሐፍ ቃላት | ፲፱ |
| ጻድቁ አባ ገሪማ | ፳ |
| የፓትርያርኮች ስም | ፳፩ |
| በመስቀሉ አዳነን | ፳፪ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

ከሁሉ አስቀድሜ የሰላም ባለ ቤት አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራችሁን እንዲያቃናላችሁ እየተመኘሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንድታብራሩልኝ አቀርባለሁ የማቀርባቸውም ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ጾም ፵ ቀን ፵ ሌሊት መሆኑ ይታወቃል እኛ ግን የምንጾመው ፶፭ ቀኖች ነው ለምን እንዲህ ሆነ?

፪ኛ/ ራእይ ም·፳፪፣፲፰ ላይ የተናገረው ስለምን ነበር ሌላ ነገር እንዳንጨምር አይደለምን ይህ ከሆነ ከጌታ ጾም ላይ ለምን ፲፭ ቀን ተጨመረ?

፫ኛ/ የይስሐቅ ልጆች ኤሳውና ያዕቆብ የክርስቲያንና የእስላም መለያዎች ናቸው ይባላል ይህስ እውነት ነውን በዚያን ጊዜ ክርስትና እና እስልምና ነበረ ወይ ይህንን አብራርታችሁ እንድትገልጹልኝ ።

በተጨማሪም የክርስትና ሃይማኖትና የእስልምና ሃይማኖት በስንት ዓ/ም እንደ ተመሠረቱ ግለጹልኝ ።

፬ኛ/ ጌታ በተወለደ ጊዜ እጅ መንሻ ዕጣን ወርቅና ከርቤ ይዘው በኮከብ እየተመሩ እጅ የነሱት ነገሥታት የየት ሀገር ናቸው?

፭ኛ/ ሕገ ኦሪት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ምን ጊዜ ነው በማን ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ግለጹልኝ ።

፮ኛ/ የሙሴ ሚስት ኢትዮጵያዊት እንደነበረች ይነገራል ግን የየት ሀገር ዜጋ ነበረች?

ዲ·ታሾመ ታዬ ከፍተኛ
[illegible] ፲፭ ቀበሌ ፳፯
አዲስ አበባ

ዲያቆን ታሾመ ታዬ ያቀረብካቸው ጥያቄዎች ጠቃሚዎችና ትምህርት ሰጭዎች በመሆናቸው እናመሰግናለን ያቀረብካቸውንም ጥያቄዎች መልስ ፤

፩ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ጾም እንደ ገለጽከው ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ነው ማቴ ፬ ቁ ፬ ግን በዓቢይ ጾም መጀመሪያ ያሉት ፰ ቀኖች ስለ ሕርቃል የተባለ ንጉሥ እንዲጾሙ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ ቀኖች ናቸው ሲጨምርዋቸውም አለ ምክንያት አልነበረም አንድ አመጸኛ ንጉሥ ተነሥቶ ክርስቲያኖችን እየለየ ይጨፈጭፍ ነበርና ይህን ጠላታችንን አጥፋልን በማለት ክርስቲያኖቹ ተሰብስበው ቢለምኑት ነፍስ አትግደል የሚል ሕግ አለ ስለዚህ እንዴት ይህንን አመጸኛውን ንጉሥ ላጠፋላችሁ እችላለሁ ቢላቸው ክርስቲያኖቹ እሱን አጥፍተህ ክርስቲያኖቹን ከእሱ እጅ አድናቸው እንጂ እኛ እንጾምልሃለን ስላሉት በዚህ ምክንያት የተመሠረተ ጾም ነው ከነስሙም ጾመ ሕርቃል ነው የሚባለው ሁለተኛም በመጨረሻ ያሉት ፯ ቀኖችም በክርስቶስ ላይ የተነሱት አይሁድ እንዲገድሉትና እንዲሰቅሉት ሲመካከሩ ሰንብተው በምክር የተስማሙባቸውና በመስቀል ሰቅለው የገደሉበት በጠቅላላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጸዋትወ መከራ የተፈጸሙበት ስሞን ስለ ሆነ ክርስቲያኖች ሁሉ እነዚህን ቀኖች በጾምና በስግደት እንዲያስቧቸው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የጨመርዋቸውና የወሰንዋቸው ስለሆነ ነው የምንጾመው እንጂ ጌታ ፶፭ ቀን ጾመ ብለን አይደለም ስለዚህ ባጭሩ ጌታ የጾመው ፵ ቀንና ሌሊት ሲሆን ፲፭ ቀኖች ግን በሊቃውንት የተጨመሩ ናቸው ።

፪ኛ/ ራእይ ፳፪፣፲፰ የጠቀስከው አለቦታው ነው የጠቀስከው ዮሐንስ በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር መቅሠፍቶች ይጨምሩበታል ያለው ለምን በጾም ላይ ጾምን ጨመራችሁ ማለቱ ሳይሆን ማንም ሰው በዚህ በራእይ ከተጻፈው ቃል ላይ ዮሐንስ በደሴተ ፍጥሞ ያየው ራእይ ይህ ብቻ አልነበረም ብሎ ሌላ ቃል ጨምሮ ቢገኝ ወይም ከዚህ በተፃፈው ቢቀንሱ መቅሠፍቶች ይጨመሩበታል ማለት ነው ። እንጂ ስለ ጾም እንዳይደለ ወይም ስለ መላ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይደለ ማወቅ አለብህ ይህ ከዚህ ቢጨምር ወይም ከዚህ ቢቀንስ የሚለው ቃል ራእየ ዮሐንስን ብቻ የሚመለከት ነው ።

፫ኛ/ በእነ ያዕቆብ ዘመን ክርስትናም እስልምናም አልነበረም ስለዚህ ያዕቆብና ኤሳው የክርስትና የእስላምና አከፋፋዮች አይደሉም ምክንያቱም ያዕቆብና ኤሳው የነበሩበት ጊዜ ወደ ሶስት ሺህ ፫ሺህ ዓ/ዓ አካባቢ ነው ።

ክርስትና የተመሠረተው ግን ፭ሺ፭፻ ዓ/ዓ ከተፈጸመ በኋላ በ፯ ዓ/ም ነው የእስልምና ሃይማኖትም የክርስትና ሃይማኖት በተመሠረተ በ፯ኛው መቶ ዘመን ነው

(ወደ ገጽ ፫ ይዞራል)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ጾም ለሰላም

እነሆ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመውን ዓቢይ ጾም ተያይዘነዋል ጾሙ ግን ለሰላም ይሁን ፡ አንላለን ባሁኑ ጊዜ የምሥራቁም ሆነ የምዕራቡ ዓለም ከሰላም ተለይቶ ከፍቅርም ተራቁቶ በላይ ላይ ያለውም ሕብረተሰቡ ሁሉ እርስ በእርሱ በአዳፍኔ እየተጨፋጨፈ ከመኖሩም በላይ በረሀብና በእርዛትም እየተገረፈ ነው ።

ከዚህም የተነሣ ዓለም እንደ ብራና ተወጥሮ የሚሆነውን አጥቶ ይገኛል ። ሰላም ሲጠፋ ፍቅርም ከገጸ ምድር ሲወገድ መሬትም በድርቅ ስትመታ የሰው ልጅ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን አጥቶ ግራ ተጋብቶ ነው የሚታየው ፡ ይሁን እንጂ በዓለም ያለው ችግር በዓለም የሚታየውም ውጣ ውረድና ውጥረት ሊጠፋ የሚችለው በጾምና ጸሎት ነበር ጾምና ጸሎት የተፈተኑ መድኃኒቶች ናቸውና ።

አንድ ፈተና በዓለም ላይ ሲያንዣብብ ሕብረተሰቡ ወደ ላይ ቢወጣ ወደ ታችም ቢወርድ ፈተናውን ለማስወገድ ችሎታ የለውም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ የችግር ዘርፎች ሁሉም ሊወገዱና ከገጸ ምድር ሊጠፉ የሚችሉት በጾምና በጸሎት ብቻ ነው ። የቀድሞ አባቶቻችን ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት መምህራንም ሆኑ ሊቃውንት አንድ ፈተና በሚያጋጥማቸው ወቅት ያንን የደረሰባቸውን ፈተና ለማስወገድ የሚይዙት መሣሪያ ጾም ነበር ። ጾምና ጸሎት የተፈቀዱ መድኃኒቶች መሆናቸውንም ለማረጋገጥ ራሱ አምላካችን ክርስቶስ ወዝንቱ ዘመድ ኢይወድእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት ይህ ባላጋራችሁ ጠላት ካልጾማችሁ ካልጸለያችሁ ሊወጣላችሁ አይችልም ብሏል ማቴ ፲፯ – ፳፩ ።

እንዲህ ከሆነ ሰላምን በዓለም ላይ ለማምጣትና ለማስፈን ጠብንና ክርክርን እነሱን የመሳሰሉትንም ሁሉንም ከገጸምድር ለማስወገድ በየጊዜው እንጾማለን በየሰዓቱም እንጸልያለን ግን ችግሩም ሆነ መከራው በፊታችን እየተደቀነ ነው የሚታየው የሚል ሰው ይኖር ይሆናል አባባሉም ልክ ነው ነገር ግን ከዚህ ላይ የምንገነዘበው ታላቁ ቁም ነገር ቢኖር በምንጾምበት ጊዜ ከንፈራችን ደርቆ ሲታይ በጸሎትም ወቅት ከንፈሮች ይንቀሳቀሳሉ ይሁን እንጂ ከእነዚህ ከንፈሮች መለየት የማይገባው የሰው ልብ ከእነሱ ተለይቶ ስለሚሄድና ከእነሱ ጋር ሕብረት ሲኖረው ነው የታሰበው ሐሳብ ከፍጻሚ ደርሶ ግቡን ሲመታ የሚታየው በዚህ በ፳ኛው መቶ ዘመን እንደሚታየው አብዛኛው ሕብረተሰብ በሚጾምበትና በሚጸልይበት ወቅት ማስወገድ የሚገባቸው ነገሮችን ሲያስወግድ ሲጾምና ሲጸልይ ይታያል እየጾመ ይሳደባል ይደባደባል እየጸለየ በወንድሙ ላይ ይዝታል ታድያ እነዚህ ሁሉ ከጾምና ከጸሎት ጋር የሚዛመዱ አይደሉምና ዋጋ አይኖራቸውም ።

ከንፈርና ልብ ከተለያዩና ካልተገናኙ ከንፈሮች ለጸሎት ሲንቀሳቀሱ ልብም በበኩሉ በሐሳብ ዓለሙን ሲያደርስ ነው የሚውለው ስለዚህ በልብ የሚታሰበው ሌላ በአፍ የሚጸለየውም ሌላ በመሆኑ የሚፈለገው ሁሉ ግቡን ሳይመታ የሚቀረው ከዚህ የተነሣ ነው ሰዎች ሁሉ እየጾሙ ከተቀየሙ እየጸለዩም ከተለያዩ ጸሎታቸውንና የጾማቸውን ዋጋ እንደማያገኙ ሲገልጽ የዓለም መድኀን ክርስቶስ ጸሎቱ ለመስተቀደም ከመ ዘርአ ዘወድቀ ማእከለ አስዋክ የቂመኛ ጸሎት በእሾክ ላይ እንደወደቀ ዘር ነው በእግዚአብሰሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም ሲል በሰፊው አስረድቷል ከእሾህ ላይ የወደቀ ዘር እንደማይረባ የታወቀ ነው ጾምም እነደዚሁ ንጽሕና በተሞላበት መንፈስ ካልጾሙት ዋጋ አይኖረውም ይህንን በመመልከት አንድ ታላቅ ሊቅ እንዲህ ብሏል ወንድምን አስቀይሞ ከመጾም ሥጋን መኮምኮም ይላል ይህን የተናገሩ ሊቀ ጾም አይጾም ጾም ይሻር ማለታቸው አይደለም የሰው ልጅ ከቂም ከበቀል ከምቀኝነት እንዲነጻና ቂምንና በቀልንም ይዞ ቢጾም በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እንደሌለው ለማስገንዘብ ነው ። ለሁንም ይህ የተያያዝነው ዓብይ ጾምን ስንጾም እነእገሌ ይጾማሉ እኔም መጾም አለብኝ በሚል ሐሳብ ሳይሆን ይጠቀመኛል መንፈሳዊውን ክብር ያሰጠኛል በሚል መንፈስ የተመሠረተ መሆን አለበት ። ሰውነታችንን በጾም ከቀጣነው ክፉው ሐሳባችንንም በጸሎት ካስወገድነው በልባችን ሰላም ይሰፍናል በመንፈስ ቅዱስም ሕይወት ይታደሳል ጨው የሌለው ምግብና ሰላም የሌለው ጾም ልዩነት የላቸውም ሁለቱም አንድ ናቸው ጨው የሌለው ምግብ ጣዕም እንደሌለውና ለመብላት እንደማያስመኝ ሰላም የሌለው ጾምም ጣዕመ ጸጋ ስለሌለውና መንፈሳዊውን ክብር ስለማያሳጣ ተርፋ ድካም ብቻ ነው ።

የሰው ልጅ በመጀመሪያ ስለ ሕይወቱና ስለ ሀገሩ በሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ስለ ጠቅላላ ሕብረተሰብ መጾምና መጸለይ ተገቢ ነው ነቢዩ ኤርምያስም ይህንን አስመልክቶ ሑሱ ሰላማ ለብሔር የሀገርን ሰላም ፈልጉ ብሏል ።

አንድ ሰው ሰላምን ከተከተለ ጸሎትንም ካዘወተረ በመንፈስ ቅዱስ ስለሚጠበቅ በማንኛውም ነገር አይወድቅም ቢወድቅም ቁሉ ፈጥኖ ይነሣል የሚጠብቁትና ቢወድቅም የሚያነሱት መላእክት ይታዘዙለታልና ። ስለዚህ ጾማችንንና ጸሎታችን ለሰላም ይሁንልን አሜን ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ስለዚህ ክርስትና እና እስልምና በእነ ያዕቆብ በእነ ኤሳው ነበረ ማለት ከባል በፊት ልጅ ይስጠኝ ማለት ይሆናል የእንቆቅልሽ አባባል ነው ።

፩ኛ/ እጅ መንሻ ይዘው ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጡት ነገሥታት ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት እምኃ ያበውኡ ነገሥተ ሳባ ወዓረብ ጋዳ ያመጽኡ ይላል እንዲህም ማለት "የተርሴስና የደሰያት ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ የሳባና የዓረብ ነገሥታትም እጅ መንሻን ያመጡለታል መዝ ፸፩፡፲ መመልከት ነው።

፪ኛ/ ሕገ ኦሪት ወደ ኢትዮጵያ የገባው የዳዊት የልጅ ልጅ በሆነው በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን በ፩ሺ ዓ/ዓ አካባቢ ነው የገባው ።

፫ኛ/ የሙሴ ሚስት አንተ ራስህ እንደ ገለጽከው ኢትዮጵያዊት ስትሆን አባትዋም ዮቶርካህነ ምድያም ይለዋል የምድያም ካህን ከሆነው ከዮቶር የተወለደች ናት በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ዙርያ ያሉት አገሮች ሁሉም በጠቅላላ ኢትዮጵያ በሚል ስም ይጠሩ ስለ ነበረ ኢትዮጵያዊት ናት ተባለች እንጂ የሙሴ ሚስት የምድያም ሰው ናት ባሁኑ ጊዜ ያች ምድያም ተብላ ትጠራ የነበረችው ሀገር ፡ ኑብያ ተብላ ትጠራለች ። ይህችም ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት ።

ከንፈርግብ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ኅልፈት

*የመሪ ጌታ ፍሥሐ ባንተን የ፴ ቀን መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ፣ ክርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሣ የተዘጋጀ የኀዘን እንጉርጉሮ ።*

ፍሥሐ ተነሳ ቤትህን ተመልከተው
ካንተ ከተለየ ፵ ቀኑ እኮ ነው ።
እንኳንስ አርባ ቀን አራት ቀንም ቢሆን
ቤት ያለባለቤት አያሟላም ሁሉን ።
በሁለት ፊደሎች የመሠረትከው ቤት
ባጡም ግድግዳውም ዘሞ ሊወድቅ ነው ፈጥነህ ድረስለት
ቤት ከመሠረቱ ከተናጋ ድንገት
እጅግ ያዳግታል መልሶ ለመሥራት ።
ቤት በሁለት ፊደል የተጻፈው ስሙ
ባልና ሚስት እንጂ ማለት ነው ትርጉሙ ።
- ከሁለቱ ፊደል አንዱ ከጎደለ
በዚያም በዚህ ቢሉ ቤት መባል የት አለ?
- ሁለቱ ፊደላት በሁለት ሲባዙ
አራት ይሆናሉ
እነዚህ ተዳምረው ተባዝተው በሙሉ
ያለ ምንም ገደብ ምድርን ይመላሉ ።
- ይህም አስቀድሞ ተጽፏል በኦሪት
አንዲት ሴት ላንድ ወንድ አንድ ወንድ ላንዲት ሴት ።
- ብዙ ለምዶ ነበር ቤቱ በፋሲካ
ባሁኑ ዘመን ግን ምንም አልተሳካ
ቀዝቅዞ አየነው ቤት ያለባለቤት
እንዲህ ኖሯል ለካ!
- ፋሲካስ አለፈ ዮሐንስ ሲመጣ
እንቁጣጣሽ ልብሱ የልጆቹ ጣጣ
ያስለመድከው ሁሉ እንደት
ሊሟላነው እስቲ ምክር ለምጣ ።
- ፍሥሐ ደህና ሁን ብዙ ተወያየን
እሱ ይከተልህ የአብርሃም ለም
ላክ ደግሞም የሰሎሞን ።

# ሆሣዕና
# "ሰላምሽ ዛሬ ነበር"

በዓለም ውስጥ ከሚኖሩ ግዙፋን ፍጥረታት ሰላምን የሚፈልጉ እጅግ ብዙዎች ሲሆኑ ሰላምን የሚቃረኑና የሚጠሉ ሰው ሁሉ በሰላም ዐርፎ እንዳይቀመጥ የላይ ፈሪ የታች ፈሪ እያሉ ሰውን ከሰው ጋር እያጋጩና እያጣሉ የሚኖሩ ደግሞ በርከት ያሉ ሰዎች እንዳሉ አይዘነጋም ክፋትና ተንኮልን ዕለታዊ ተግባር አድርገው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ የሚዘዋወሩ ስፍር ቁጥር የላቸውም ።

ዓለም ከሰላም ተለይታ ከመንፈሳዊ ፍቅርም ተራቁታና ነጻነትዋን አጥታ በየዘመኑ ስትንከራተት በኖረችበት ወቅት እንደዚሁም የበደለንም ያልበደለውንም ሞት ይገዛው በነበረበት ጊዜ ሰማያዊ ጌታ ለዚህ ለተጐዳው ዓለም ለማሻሻል ነጻነቱን ላጣ ነጻነቱን ሰላምን ላጣም ሰላሙን ለመስጠትና ለሁሉም እንደፍላጐቱ ለማደል ወደ ዓለም መጣ ይሁን እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከሞት መንጋጋ ፈልቅቆ ለማላቀቅ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ታላቋ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ሰላምን የተጠሙ ሰዎች የሰሌንን ዝንጣፊ ይዘው ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እያሉ የሚያስደንቅ መዝሙር እየዘመሩ በታላቅ ክብርና አክብሮት ሲቀበሉት ፤

ሰላምን የማይፈልጉና የሰላም ባላንጣዎች አይሁድ ግን ባዩት ክብርና በሰሙት አስደናቂ መዝሙር በመንፈስ ቅንዓት ስለተበከሉ ከቅንዓታቸው የተነሣ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተደረገለት ታላቅ አቀባበል እንደ እሳት ስላቃጠላቸው ሳያፍሩ በድፍረት እነዚህ ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት እያሉ የሚዘምሩትን ዝም በሉ አትላችውም? በማለት ቃላቸውን ከፍ አድርገው ተናገሩት

ምቀኝነታቸውና ተንኮላቸውን ንዴታቸውን ያወቀና ንዴታቸውን የተገነዘበ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በበለጠ እንዲቃጠሉና ስሕተታቸውንም እንዲያውቁ በእነዚህ በሚዘምሩት ላይ ከተመቀኛችሁ እነዚህ ድንጋዮች ሊዘምሩ ይችላሉ የሚል መልስ ሰጣቸው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ መልክ ወደ ታላቋ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ከተማይቱን አይቶ አዘነላት ፤

እርግጥ ያዘነው በከተማይቱ የተሠሩ ቤቶች ባለማማራቸው ወይም የከተማይቱ ቅጽር ያልጠበቀ ሁኖ በማየቱ አልነበረም ከተማይቱን አይቶ አዘነላት ማለት በውስጥዋ የነበሩ ሰዎች በመንፈሳዊ ተግባር የማይመሩ አቅዋማቸው ሁሉ የተበላሸ ሁኖ በማየቱ ነበር ።

ይህንም በመመልከቱ ወደ ከተማይቱ ወደ ኢየሩሳሌም እየተመለከተ (ሶበሰ ተአምሪ) አላወቅሽም እንጂ አውቀሽስ ቢሆን ኑሮ ሰላምሽ ዛሬ ነበር ዳሩ ግን ምን ይሆናል ሰላምሽን አላወቅሽም አለ ። በከተማይቱ አስጠግቶ ሕዝቡን መውቀሱ ነው የሰላም ባለቤት ክርስቶስ ሰላሙን ይዞ ሲመጣ በሰላም መቀበል ለሰው ልጆች ግዴታቸው ነበር ነገር ግን አንዳንዶቹ በክብር ሲቀበሉት የሰሌን ዝንጣፊ ይዞ እየዘመሩ ቢቀበሉትም አንዳንዶቹ ግን ዓይናቸው እንደቀላና የመዝሙሩም ጣዕም ኮሶ ሁኖ እንደታያቸው ያመለክታል ወደ ወገኖቹ መጣ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም ሲል የተጻፈውም ከዚህ የተነሣ ነው ።

የሰላም ባላንጣዎች ማኅበረ አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሰላም ባለመቀበላቸው ዘለዓለም ሲወቀሱ ይኖራሉ ።

ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሰላም ያልተቀበሉት አይሁድ ብቻ ናቸውን ባሁኑ ጊዜስ ክርስቶስን የሚያሳድዱ የሉም ማለት ነውን? ምናልባት አንዳንድ የዋሆች የክርስቶስ ጠላቶች አይሁድን ብቻ አድርጎ የሚገምት ይኖር ይሆናል ግን አይደለም አሁንም ቢሆን በክርስቶስ የማያምኑ ክርስቶስን የሚያሳድዱ ሞልተዋል ።

እንዲያውም የክርስቶስ ጠላቶች መኖራቸውን የተገነዘበ ወንጌላዊው ዮሐንስ በ፪ኛው መልእክቱ በቁጥር ፰ ላይ ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጡ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ለሚመጣ ሁሉ በክርስቶስ ትምህርት የማይኖር ሰው አምላክ የለውም ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት ብሏል ። ከዚህም ላይ ሊታለፍ የማይቻል አንድ ጉዳይ አለ ይኸውም እያንዳንዱ ሰው እኔ ሰላማዊና ሃይማኖታዊ ነኝ ባይ ነው እውነትም የሚታየው ሃይማኖታዊና ሰላማዊ መስሎ ነው ። ክርስቲያናዊም ሆነ ሌላም በሃይማኖቱ የማይኮራ አንድም አይገኝም ይሁን እንጂ የወርቅ ፤ ግብዝነትና ንጹሕነት የሚታወቀው በእሳት ከተፈተነ በኋላ እንደ ሆነ ሁሉ የሰው ልጅም ሃይማኖታዊና ሰላማዊ መሆኑ የሚታወቀውና የሚመዘነው ባለው አቅዋም በአካሄዱና በአነጋገሩ ለሰላም ያለውም ፍላጎትና በሚያደርገው ጥረት ነው የሚለካው እንጂ ሃይማኖት አለኝ በሰላምም የምመራ ሰው ነኝ የሚለውን አነጋገር በሥራ ካልተተረጐመ ዋጋ አይኖረውም ተቀባይነትም የለውም ሰላማዊውን ሕዝብ የሚያቃቅርና በሕዝብም መካከል ጠብንና ጥላቻን የሚያዘምት የነገር እንክርዳድን የሚዘራ ከሆነ ሃይማኖት አለው ሰላማዊም ነው ለማለት አይቻልም ።

ምክንያቱም ሃይማኖት ካለ ሰላምም አለ ሃይማኖት ከሌለ ግን ሰላምም ስለማይኖር ነው ሃይማኖትና ሰላም ሁለቱም እንደ ሰንሰለት የተያያዙ ናቸውና ።

የሰላም ባለቤት አምላካችን ክርስቶስም ኃያል አምላክ ሲሆን ደካማ መስሎ መታየቱ ሰላምን ለማምጣት ነውና ሰላም የተለየው ሰው ሃይማኖቱም የላላ ነው ለማለት ይቻላል ። ባሁኑ ጊዜ እንደምናየውና እንደምንመለከተው ሁሉም እንደ ውሾች እርስ በእርሳቸው ሲናከሱና ሲፋጁ ነው የሚታዩት እንግዲህ የክርስቶስ ተከታይ በሆነ ሰው ላይ የዚህ ዓይነት ጠባይ ሊታይበት ይችላል ወይ፣ ይህንን የተገነዘበና በእስተዋይ ልቡና የተመለከተ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም እመሰ በበይናቲክሙ ትትባልዑ ወትተናሰኩ ተሐልቆ ተርፈክሙ" እንዲህስ እርስ በእርሳችሁ የምትፋጁና የምትናከሱ ከሆናችሁ እርስ በእርሳችሁ መተላለቅና መተራረድ ቀረባችሁ ብሏል ገላ ፭–

ሐዋርያው እንደተናገረው አሁንም ቢሆን መተላለቅና መተራረድ ነው የቀረው ለመሆኑ ይህ የጳውሎስ መልእክት ማንን የሚመለከት ይምስላችኋል እስቲ እና ስተውለው እስቲ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ለማን ስለእነማን እንደ ተናገረው እንመርምረው ። እርግጥ እያንዳንዱ በግል ቢጠየቅ እኔን አይመለከትም የሚል እንጂ ይህስ እኔን የሚመለከት ይመስላል የሚል አንድም እንደማይገኝ የታወቀ ነው ነገር ግን ላስተዋለው ሰው የሚያከራክር መስሎ አይታየኝም ሥራው ግልጥ ነው የሆነ ሁኖ ሁሉን ትቶ የራቀውን ለማቅረብ የተበተነውን ለመሰብሰብ ያዘነውን ለማጽናናት የተበሳጨውንም ለማረጋጋት ሲባል ሁሉም ሰላምን መያዝ ያስፈልጋል ሰላምን መከታተል ማሰብ ነው ሰላም የሕይወት ቁልፍ ነውና ።

ከነፈርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

# ጸሎተ ሐሙስ/ የቀን ቅዱስ ፡

ይህ ቀን ሙሉ አገልግሎት የተሰጠበትና እራስን ዝቅ የማድረግ ትህትና የተፈጸመበት በመሆኑ ጸሎተ ሐሙስ የቀን ቅዱስና የሥራ ቀን መሆኑን ታሪክ ሲያስታውሰን ይኖራል ። ይኸውም አሮጌ የነበሩት አምስቱ የመሥዋዕት ዓይነቶች የተሻሩበት አርጅቶና አፍጅቶ የነበረውም የቤተመቅደስና የምኩራብ ሥርዓት የተወገደበት አዲስ መሥዋዕትና ሥርዓት የተተከበት ምግባረ ሠናይ የታየበትና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ እራት ያበላበት በጌቴሴማኒ መዝሙር የተዘመረበትና ጸሎትና ስግደት የቀረበበት ክርስቶስ ለመስቀል ሞት የተዘጋጀበት በመሆኑ ሐሙስ የቀን ቅዱስ የሚለውን መልካም ስም ሊያገኝ ችሏል ። ከላይ የተጠቀሱትን በመጠኑ ዘርዝረን እናሳያለን ።

ሀ/ የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቃጠል መሥዋዕት የሚባለው በመሠዊያው ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት እሳቱ ከበላው በኋላ አመዱን አንስቶ በመሠዊያው አጠገብ ያፈስሰዋል ፡ አመዱንም ተሸክሞ ከሰፈሩ ንፁህ ሥፍራ ወደ ሆነው ወደ ውጭ አውጥቶ ይጥለው ነበር ። ኦሪት ዘሌዋውያን ም·፮·፲-፲፩

ለ/ የእህል ቁርባን የእህል ቁርባን አቀራረብ ደግሞ የአሮን ልጆች በእግዚአብሔር ፊት በመሠዊያው ፊት ያቀርቡታል ካህኑም ከእህሉ ቁርባን መልካሙን ዱቄት ከዘይት ጋር እፍኝ ሙሉ ደግሞም በእህሉ ቁርባን ላይ ያለውን ዕጣን ሁሉ ያነሣል ። ኦሪት ዘሌዋ· ፮ ፡ ፲፬-፲፰

ሐ/ የደኅንነት መሥዋዕት የደኅንነት መሥዋዕት የሚባለው ሠውተው ወደ እግዚአብሔር አመልክተው ከአባር ከቸነፈር የሚድኑበት ነበር መሥዋዕቱም የሚሠዋው መከራው በደረሰባቸው ጊዜ ብቻ ነው ኦሪት ዘሌዋ· ፫ ፡፩-፫ ።

መ/ የኃጢአት መሥዋዕት የኃጢአት መሥዋዕት ማለት ሠውተው አፍአዊ ኃጢአትን የሚያስተሰርዩበት ነው ኦሪት ዘሌ·ምዕ ·፬·፩ -፫

ሠ/ የበደል መሥዋዕት የበደል መሥዋዕት የሚባለው ሕዝቡ በደላቸውን ጥፋታቸውን ለካህናቱ ነግረው ንስሐ የሚቀበሉበት ነው ኦሪት ዘሌ·ም· ፭ ፡፩-፯

የመሥዋዕቱ አቀራረብ ከእንስሳት ወገን የሆነ እንደሆነ ደግሞ እንስሳው ንፁህ የሆነ እንከን የሌለበት ሲሆን ካህኑም ሁለቱን እጆቹን በሕያው እንስሳ ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእሥራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢአታቸውንም ሁሉ የአቅራቢውንም ኃጢአት ጭምር ይናዘዛል በመጨረሻም በእንስሳው ራስ ላይ ያሸክመዋል ። ባወጣው ሰውም እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል ። ኦሪት ዘሌ·ም· ፲፮ ፡ ፳፩ እንስሳውም ኃጢአቱን እንደ ተሸከመ ወደ በረሃ ከሄደ በኋላ የአውሬ እራት ሆኖ ይቀር ነበር እነዚህ ሁሉ መሥዋዕቶች ቢቀርቡም ምሳሌ እንጂ አማናዊ አልነበሩም ብዛትና ዓይነትም ቢኖራቸው ጥራት አልነበራቸውም መርገመ ሥጋንና መርገመ ነፍስን ሊያስወግዱ ካለመቻላቸውም በላይ እውነተኛው መሥዋእት ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ መቆያ ሆነው የሚጠባበቁ ጊዜያዊ ድርጊቶች ነበሩ ጉድለታቸው ይህ ብቻ አልነበረም ሀብታምንና ድሀን ከማራራቃቸውም ሌላ ለሕዝቡ እኩልነትንና አንድነትን ስለማይሰጡ ሰላምና ፍቅርን አያስገኙም በረከትም አያውርዱም ነበር ።

ከዚህም የተነሣ አዲስ መሥዋዕትና አዲስ ሥነ ሥርዓት በማስፈለጉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ የፋሲካ በግ እና አዲስ መሥዋዕት አድርጎ እራሱን በጸሎተ ሐሙስ አቀረበ የሰውንም ኃጢአት ሁሉ እራሱ ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ በረሃ ተጓዘ ይህንንም በማድረጉ አሮጌ የነበረው የሰው ሕይወት ታድሶ **ከፍተኛ ለውጥ ሊያገኝ ቻለ ።**

በሥጋዊ ዓለም የተለያዩና የሚለዋወጡ ሥርዓቶች እንደነበሩ ሁሉ በመንፈሳዊ ዓለም በኩል ግን የተለያዩ የሥርዓት ዘመናት **ቢኖሩም የተሐድሶ ለውጥ ታይቶ**ባቸው አይታወቅም ነበር ። ስለዚህ በጸሎተ ሐሙስ አዲስ ሥነ ሥርዓት ከአያሌ ለውጥ ጋር መንፈሳዊ ተሐድሶ ጭምር በጉልህ ለመታየት በቅቷል ። ይህም ድርጊት ለአዲሱ መስዋዕትና ሥርዓት መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ ተገኘ ።

ለምሳሌ በጊዜው ለምልሞና አብቦ ይታይ የነበረው ዛፍ ጊዜው ሲያልፍበት ቅጠሉና አበባው **ተራግፎ እርቃኑን እንደሚቀር** ሁሉ ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው አሮጌው የኦሪቱ ሥርዓት ጊዜው ስላለፈበት በውስጡ ተሸክሟቸው የነበሩት አሮጌዎች መመሪያዎችና መተዳደሪያዎች ሁሉ እየተራገፉ በመውደቃቸው ሌሎች ለአዲሱ ሥርዓት ምቹ የሆኑ ለውጦች በቦታው ተተክተውበታል ። በዚህ አኳኋን ጸሎተ ሐሙስ ባለፈው ሥርዓት ውስጥ የነበረውን የፋሲካን ሥርዓት የሻረና ለአዲሱ ሥርዓት ከፍተኛ ቦታ የሰጠ በመሆኑ ታላቅ የለውጥ ቀን ሊሆን ችሏል ። በዚሁ ዕለት የአዲሱ ሥርዓት ጀማሪ የሆነው ክርስቶስ ባጭር ታጥቆ ራሱን ዝቅ አድርጎ የተከታዮቹን እግር አጥቦ በቃል የገለፀውንና ያስተማረውን በተግባር ተረጎመው ይህ አስደናቂ ለውጥ ሲደረግ ለጊዜው የለውጡ መንፈስ ያልገባው ጴጥሮስ ግን ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ እግር ማጠቡን በከፍተኛ መንፈስ ተቃውሞ ነበር ሆኖም ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር አንድነት ማህበራዊ ሕይወት የለህም አለው የአዲሱ ሥርዓት ተቃዋሚ የነበረው ጴጥሮስም የለውጡን መንፈስ ፈፅሞ ስለተረዳ ይህ ከሆነ እግሬንም ብቻ ሣይሆን ራሴንና እጄን ሁሉ እጠበኝ ሲል መላ ሰውነቱ በአዲስ ሥርዓት እንዲታጠብለት ጠየቀ እንደ ጥያቄውም ተፈፀመለት ።

ይህ ሁሉ ምግባረ ሠናይ የተፈጸመው መጋቢት ፳፯ ቀን ፴፫ ዓ·ም ሲሆን ከተፈፀሙትም ተግባሮች ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀመዛሙርቱን እግር ያጠበበት ቅዱስ እራት **ያበላበት በጌቴ ሴማኒ አያሌ ስግደ**ትና ጸሎት የፈፀመበት ሁሉ እኩል የሆነበት ጌታ ራሱን ዝቅ ያደረገበት ሎሌ ራሱን ከፍ ያደረገበት የእኩልነት መንፈስ በጌታችንና በአምላካችን የታወጀበት ዕለት ሐሙስ የተቀደሰ ዕለት



# ዲያብሎስ ታሠረ

በዚህች ምድር ላይ ለሚገኙ መላ የሰው ዘሮች ለምድራዊውም ሆነ ሰማያዊ ሕይወታችው ዓይነተኛ መሰናክል ሁኖ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ አመታት ያህል የኖረው ዲያብሎስ በሕያው አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ለሰው ልጆች መሰናክል ከነበረው ሥልጣኑ ተሽሮአል ።

በመጽሐፈ ኢሳይያስ በምዕ·፲፬ ቁ ፲፪ ላይ "አንተ የንጋት አጥቢያ ኮከብ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ አሕዛብን ያዋረድህ አንተ ሆይ እንዴት እስከምድር ድረስ ተቆረጥህ ። ……… በሰሜን ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ከደመናዎችም ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ ነገር ግን ወደሲኦል ወደጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ" ተብሎ እንደተመዘገበው በመጀመሪያ የመላእክት አለቃ የነበረው ዲያብሎስ በአደረበት ትዕቢት ከነበረው ሥልጣን መዋረዱን እንረዳለን ።

በኋላ ግን እግዚአብሔር አምላክ በአርአያውና በምሳሌው የፈጠረው አዳም በዲያብሎስ አነሳሽነት ሕገ እግዚአብሔርን ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ በሰው ልጆች ላይ ሰይጣን ነግሦ ሰዎችን ከሕይወት ወደሞት አዘቅት ይመራ ነበር ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በ፩ኛ ቆሮ ምዕ ፲፭ ቁ፶፫-፶፯ በጻፈው መልዕክቱ ላይ "ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ሽሮአል የሞት ፍርሃትንና መውጊያን አስወግዷል በማለት ያስረዳል ።

በአበው ነቢያት የተነገረው የድህነት ፍጻሜ ዘመን ሲደርስ እግዚአብሔር ወልድ ከቅ/ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሁኖ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረ ጊዜ በሰው ልጅ ላይ ሰፍኖ የነበረውን የኃጢአት መርገም በመስቀሉ እንደሚያስወግድና የዲያብሎስንም ሥልጣኑ ሞት እንደሚሽር በማይታበለው አምላካዊ ቃሉ ሲገልጽ "አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሷል የዚህም ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል ።" ሲል በዮሐ·ራዕይ ፲፪·፴፩ በተናገረው እንረዳለን ።

ሐዋርያው ዮሐንስም በ፩ኛ

መሆኑን ያሳስበናል ።

ይህም ኢሳይያስ በትንቢቱ ምዕራፍ ፶፫ ፡፯ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በጠላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም ሲል የተናገረው ፍሬ ነገር የፋሲካ በግ መሆኑን ያስረዳል ። ወንጌላዊው ዮሐንስም በምዕራፍ ፩ ፡ ፳፱ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ በማለት ስለዓለም ኃጢአት የሚሠዋ እውነተኛ በግ መሆኑን ገልጿል ።

እንደተባለውም በክርስቶስ ፋሲካነት ከሥርዓተ ኦሪት ወደ አዲስ ሥርዓተ ወንጌል ተሸጋግረናል ማለት ነው ይህ ከሆነ ክርስቶስ ጴጥሮስን እኔ ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር ክፍል የለህም ያለውን ቃል እያስታወስን በለውጡ ሥርዓት ከአሮጌው ሕይወታችን ልንታጠብ ያስፈልጋል ። ስለ እኛ የተሰዋውንም የፋሲካውን በግ ሥጋና ደም ተቀብለን አሮጌ ሕይወታችን በአዲስ ሕይወት መለወጥ ቁም ነገሩ ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

መልዕክቱ ምዕ ፫ ቁ ፰ ላይ "ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ" በማለት እንደገለጸው የሰዎችን ውርደትና ጉስቁልና የተመለከተ እውነተኛው የሰው ወዳጅ ሕያው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳም በበደለ ራሱን ለሰው ልጆች ካሣ አድርጎ በመስጠቱ የዲያብሎስ ሥልጣን ታግዶአል በኃጢአት ፈንታ ጽድቅ በመረገም ፈንታ በረከት ተተክቶአል።

ስለዚህ ነበር ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትዕዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ደብዳቤ ደመሰሰው እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል ። አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሣት በግልጥ አሳያቸው" በማለት ለቆላስይስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልዕክቱ ላይ በምዕ ፪ ቁ ፲፬ የገለጸው ።

ሐዋርያው በዚህ መልዕክቱ ላይ በግልጽ እንደመዘገበው ጌታ ሰው ከመሆኑ በፊት ለአያሌ ዓመታት ዲያብሎስ የሰው ልጆችን በጽድቅ ፈንታ ኃጢአትን እያሠራ ከሰዎች ወደሰዎች ይተላለፍ በነበረው የኃጢአት ቁራኝነት አሥሮ በመያዝ በፍዳ ከአቆየው በኋላ በኋላ ዘመን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የኃጢአት ቁራኝነት ከሰው ዘሮች ላይ መደምሰሱንና ለመጨረሻ ጊዜ መሰረዙን እንረዳለን ።

እንግዲህ ከላይ በተገለጠውና በአያሌ ቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ እንደሚገኘው ቀድሞ በአደረበት ትዕቢት ከመዓርጉ ከክብሩ ተዋርዶ ምድረ ፋይድ የወረደው ዲያብሎስ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል "ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን" አንተ ሰይጣን ከፊቴ ወግድ ማለትም በእኔ ከሚአምኑት ክርስቲያኖች ፊት ለምንጊዜም ወግድ ተብሎ መባረሩን እንገነዘባለን ።

ዲያብሎስ ከምዕመናን በፊት በመባረርና የበደል ዕዳ በመሠረዙ ሕማምና ሞት የሌለባት ፍጹም ደስታ የሰፈነባት ዘለዓለማዊት ሕይወት ለመላው የሰው ዘሮች መሆኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ተረጋግጦአል ።

ዲያብሎስ ከሥልጣኑ ተሽሮ መታሠሩን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ያረጋገጠች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታን የስቅለት በዓል አክብራ በዋለች ማግሥት በየዓመቱ ዲያብሎስ ታሠረ ጌታ ተመረመረ በማለት ፍጹም ደስታና ዘለዓለማዊ ሰላም የተመላበትን የምሥ**ራች ቃል ስታሰማ ትኖራለች ።**

እግዚአብሔር አምላክ ዳግመኛ በሚመጣ ጊዜ በእውነተኛ ፍርዱ "ሑሩ እምኔየ ውስተ እሳት ዘለዓለም ዘድልው ለሰይጣን ወለመላዕክቲሁ እናንተ ረጉማን እስ ቀድሞ ለሰይጣን ለመላዕክቶች ወደተዘጋጀው የዘለዓለም መከራ ሂዱ በማለት የሚሰጠውና ሕገ እግዚአብሔርን በማያከብሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸመው ቃል በእኛ ላይ እንዳይደርስብን ቂምና በቀልን በአጠቃላይ ክፉ ሥራ ሁሉ የዲያብሎስ መሆኑን ተገንዝበን መጥፎ ነገሮችን ከማድረግ መቆጠብ አለብን ።

ስለዚህ ከማንኛውም ሠይጣናዊ የበደል ሥራ እርቀን ሕማምና ሞት የሌለበትን የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበትን አዲስ ሰማያዊ ዓለም ለመውረስ የመልካም ሥነ ምግባር ባለቤት እንሁን ።

መሪጌታ ኢፍሬም በየነ

# የሰላም አዳራሽ

ሰላም ፍቅርንና አንድነትን የሚፈጥር የሕይወት መሠረት ነው ሰላምን የማይመኝ ሰብአዊ ፍጡር የለም ።

ይህም በመሆኑ በጥንታዊነቱና በታሪካዊነቱ በታወቀው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቅጽረ ግቢ በሥፋትም ሆነ በአቀማመጥ አስደሳችና ግሩም የሆነ አዳራሽ ተሠርቷል ።

ይህም በብዙ ወጭ የተሠራው ታላቁ አዳራሽ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰበካ ጉባኤ ምእመናንን በማግባባትና የሰበካውን ሕዝብ በማስተባበር ነው ። አዳራሹ ሰፊና ብዙ ሊቃውንትን ለማስተናገድ የሚችል በመሆኑ ከጥር ፰ ቀን እስከ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. የተካሄደው የሰላም መንፈሳዊ ጉባኤ በዚሁ ውስጥ ነበር በመሆኑም ፩ኛ ወንጌል የሚሰበከበትና ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል የሚማሩበት ። ፪ኛ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለመንፈሳዊ ጉዳይ የሚሰበሰቡበት ነው በዚሁም ሁኔታ የሰላም ጉባኤ ሲካሄድበት ስንብቶ መንፈሳዊና የሰላም ፍሬ በዚሁ አዳራሽ ስለተገኘበት የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰበካ ጉባኤ አባላት የሰላም አዳራሽ ተብሎ እንዲጠራላቸው ባቀረቡት ማሳሰቢያ ብቻ ሳይሆን የአዳራሹን ስፋትና ማማር ተመልክቶ የሰበካ ጉባኤ አባላትም ከባድ የሥራ መሥዋዕትንና በርካታ ገንዘብ ወጭ አድርገው መሥራታቸውን በመገንዘብ አዳራሹ የሰላም አዳራሽ ተብሎ እንዲጠራ በቅዱስ ሲኖዶስ ተሰይ**ሟል ። ከጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ጀምሮ በደብዳቤ አስታ**ውቋል ።

አዎ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰበካ ጉባኤ አባላት ሐሳብና ከባድ ጥረት የተሠራው አዳራሽ እጅግ የሚያስመሰግን ሲሆን ሥራው ለሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ታላቅ አርአያ ሁኖ የሚጠቀስ ነው ።

ከሰው ልጅም የሚጠበቀው ኃላፊነት ይኸው ሠርቶ ማለፍ ብቻ ነው ። ሁሉም በተሰጠው ኃላፊነት አንዳንድ ሥራ ሠርቶ ከተገኘ በእሱ ተተክቶ በሥራው እየገባም እንዲሠራ ግድ ያስገድደዋል እነ እገሌ ይህንን ሥራ ከሠሩ እኔም ይህንን ሥራ መሥራት ይኖርብኛል ወደሚለው መንፈስ እንዲያዘነብል ያደርገዋል ማለት ነው።

ቀዋሚ ሥራ ሠርቶ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ፩ኛ እገሌ የሠራው ነው እየተባለ ስሙ ሲጠራ ይኖራል ። ፪ኛም የተሠራው ሥራ ለመጭው ትውልድ ስለሚያገለግል ሁሉም ዓቅሙ በሚፈቅድለት መጠን መሥራት ይፈለግበታል የዚህ ዓይነት ሥራ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ቢቀጥል መልካም ነው እንላለን በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስም ይህንን አስደሳች ሥራ ሠርታችሁ በመገኘታችሁ ፡ የሠራችሁት ሥራ ከሚያስመሰግናችሁም ሌላ መልካም ሥራችሁን ስላየን በመላ የገነተ **ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አስተዳደርና**

**የሰበካ ጉባኤ አባላትን ሳናመሰግንናቸው አናልፍም ።**

የማይመሰገን የማይሠራ ብቻ ነው እንጂ ሠራተኛ ሁልጊዜ እንደ ተመሰገነ ነው ። የሚኖር ወዳጅ ቀርቶ ጠላቱ እንኳን ሳየቀር በሥራው ሳያመሰግነው አይቀርም ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

# ተጠበቁ አትደንግጡ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ለክርስቲያኖች ባስተማርን ትምህርት የዓለም ምንነት ፡ የዓለምን ዘለዓለማዊም ሆነ የመጨረሻ የዓለም ኅል**ፈት ከመፈጸሙ በፊት የሚታዩ ክስተቶችን የዛሬ ፪ሺ ዘመናት ገደማ ላይ ገልጾልናል ፤ ይህንንም ማቴ ም ·፳፬ ማርቆስ ም·፲፫ ሉቃስ ፳፩–፳፮ በስፋት መመልከት ይቻላል ።**

ለዓለማችን ተፈጻሚነት መድረስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ደቀመዛሙርቱ የመምጣትህ ምልክት ምን ይሆናል ብለው በጠየቁት ጊዜ ጌታ ሰጥቷቸው የነበረው መልስ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስቷቸዋል ሲል ነግሯቸዋል ።

በዘመናችን እንኳን በቅርቡ በአፍሪቃ ምድር ውስጥ በኬንያ እኔ እግዚአብሔር ነኝ በማለት ተነስቶ የነበረው ሐሰተኛ መሢህም ብዙዎችን እንዳሳተና የዚህም የስብከት ውሸንፍር እስከ ሀገራችን ድረስ ዘልቆ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው ።

በዚህ ብቻ መወሰን አይኖርብንም የወንጌልን ትምህርት በመሰላቸው በመተርጎም ቃሉን በመለወጥ ትምህርቱን በማዛባት ለማሳሳት የተነሱ ሐሰተኞች የሆኑ ወንጌለኞች ሳይሆኑ የወንጌል ወንጀለኞች ተከስተዋል ።

ከነዚህ ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን እንዳያስቱን መጠንቀቅ አለብን ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመምጣቱን ምልክት የዓለምን ህልፈት ምን እንደሆነ ትኩረት በሰጠበት ጊዜ የዘመናችንን ሁኔታ በግልጽ እንዳስተማረው ጦርንም የጦርነት ወሬንም ትሰሙ ዘንድ አላችሁ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ አትደንግጡ በማለት የሰጠንን ትምህርታዊ ኃይለ ቃል ከዘመናችን ጋር አጣጥመን ስንመለከተው ዛሬ ዓለማችንን ይህ የጌታ ትምህርት ትንቢታዊ መልህክቱም በግልጽ የቀረበ ይመስላል ስለእዚህ በእምነታችንና በሃይማኖታችን መጠንቀቅ አለብን ።

ከመደንገጥም ተጠብቀን እውነተኛውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት መከታተል መንፈሳዊ ግዴታችን ነው ብዙዎቻችን የኖርንበትን ያህል የመኖር ዕድል የለንም ይህንን በግልጽ ከተገነዘብን ተበቁ አትደንግጡ ያለው ቃል በያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ተቀርጾ ጠንካራ ክርስቲያኖች መሆን አለብን ለሚያልፈው ሕይወታችን በሚያልፉት አሳሳቾች የዘለዓለም ፍዳን መቀበል አይኖርብንም ።

ለመከራ ብንዳረግ እንኳን አለ**ፈንም ብንሰጥ ብንገደልም ይህ** ቃሉ ነውና ስለስሙ ብንጠላም





www.ethiopianorthodox.org

ውድና ክቡር ዘለዓለማዊ ለሆነው ክርስቶስ እርሱ ሕይወቱን መሥዋዕት እንዳደረገልን እኛም አልፈን መስጠት ስለሃይማኖታችን በጽኑዕ አቋም ላይ መመሥረት አለብን ጌታችን በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ያስተማረው ይህንን ነው ዛሬ በዓለማችን ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት እኛን ለማሳሳት እኛን ከሃይማኖታችን ለማዛባት የተነሱበት ጊዜ ነው ትናንት አብያተ ክርስቲያናትንን የመዘበሩ ፡ ያጠፉ ህልውናችንን በግልጽ የተቃወሙ የምሥጢር ተንኮላቸውን ደብቀው ሕጋውያን መስለው ቀርበው ሕግን ሲያጠፉ የነበሩ እነርሱ አስቀድመው ጠፍተዋል ።

ዛሬ በሰዎች መካከል ፍቅር ስለቀዘቀዘች ዓለም መግባባት አጥቷል ይህ የማይቀር ግዴታ ነውና እስከመጨረሻ በቃሉ ፀንቶ የቆየ ርሱ ይድናል በማለት ያስተማረን በመሆኑ በእምነታችን ፀንተን በሃይማኖታችን ተጠናክረን ሳንሳሳት ጠንክረን መቋቋም ከቻልን የመከራ ክስተትም እንደሚታይ መጻሕፍት ይናገራሉ።

በዚያን ዘመን ስለሕዝብህ **ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ** ሚካኤል ይነሳል ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመንይሆናል በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደእረፍትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ።

ዳንኤል ሆይ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ መጽሐፉንም አትም ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ ዕውቀትም ይበዛል ዳንኤል ፲፪ ፡ ፩ ፡ ፬ ።

ከዚህ በላይ በሙሉ ኃይለ ቃሉ እንዳለ ተጠቅሷል በዚህ ቃል **እግዚአብሔርን የአከበሩ የተገዙ እንደሚድኑ በአንጻሩም ደግሞ ተቃራኒ ወገንም በአንጻሩ ሆነው ለሚገኙት የመከራ ዘመን እንደሚሆንባቸው ያመለክታል ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሆነ ትዕዛዙን ለሚያከብር ሥርዓቱን ለሚጠብቅ ደግሞ እንደሚድን በፍርድ እንደሚያውቁስ ያስተምረናል ።**

በጌታ ምጽዓት ጊዜ አንቀላፍተው በምድር ውስጥ ትቢያ ሆነው የቀሩት ይነሳሉ በፍርድም ቀርበው ሕግ አክብረው የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት ወደ ዘለዓለም ሕይወት ተዛውረው ለጽድቅ ይጠራሉ የዚህ አቋም ተፃራሪ የሆኑት ደግሞ በሚያሳፍርና በከባድ ወቀሳ ወደ ዘለዓለማዊ ግዞት ሥር እንዲወድቁ ይደረጋሉ ።

ከእዚህ ግን ይሰውረን ይህች ዓለም በጊዜያዊነት የምናርፍባት ሠርተን በጽድቅ ወይንም በኩነኔ የሥራችንን የፍርድ ዋጋ የምንቀበልባት ዓለም ናት ። ስለዚህ **ለዚህች ኀልፊት ለሚቆራኛት** ዓለም እምብዛም አትጨነቅ በዚህ ዓለም ክብሮና ተደስቶ ከመኖር በዚህ ዓለም ደህይቶና ተቸግሮ በመኖር ለፍጻሜው የመንፈስና የጽድቅ ከበርቴ መሆን ይመረጣል ።

እውነትን ለመናገር ያህል በዚህ ዓለም እውነት ከሠራን ስለእውነት ከመሰከርን ከመኖር ይልቅ የሞት ተስፋ የበለጠ ይጠበቃል ፡ በሞት ሕልውና ውስጥ በምንካተትበት ጊዜ ኃጢአትም ጽድቅም ለመኖሩ ለእውነተኛ ሰዎች በዓለም ውስጥ ኑሮዋቸው እውነት ከሠሩ ደግሞ ክፋትን ሳያክሉበት ለፍርድ ቆይታቸው እስከሚጠሩበት በመቃብር ሆነው ጊዜያቸውን በተስፋ መጠበቁ በጣም ይቀልላቸዋል ።

ያም ሆኖ እንኳን ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ ማክበር ፈርቶ መፈጸም ለታላቁ ጽድቅ ያበቃል በዓለም ፊትም ቢሆን በረከት ታድላለች ።

እግዚአብሔር በረከት ባለጠጋ ታደርጋለችና ምሳ ፲— ፳፪ ይህ ማለት ደግሞ በዚህ ዓለምም ተድላ ደስታን በማጎናጸፍ ለፍርድ ጊዜም ከእግዚአብሔር የበረከት ፍሬን እንደምታስጥ ማወቅ ይኖርብናል ።

ሰሎሞን እንዳለው ክፉ ሰው እጅ በእጅ ሳይቀጣ አይቀርም የጻድቃን ዘር ግን ይድናል ያለውም የፍርድን የምፅዓትን ቀን በመመልከት ነው ።

ምሳ ፲፩ · ፳፩ · ፳፪ ስለዚህ በዚህች ማረፊያ እንጅ መኖሪያ ባልሆነች ፍርድ በምንጠብቅባት ዓለም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽመን ራሳችንን ለመጥቀም ወደ ጽድቅ መንገድም ለመመራት ያብቃን ።

በፍርድ ቀን ደስተኞች ለመሆን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ስለ ዚህ እውነትን ሕግን አምልኮትን ይዛችሁ ተጠበቁ አትደንግጡ ።



## ዜና ሊቃውንት

# የመሪጌታ ፍሥሐ ባንተ አጭር የሕይወት ታሪክ

መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ ከአባታቸው ቄስ ባንተ ገብረ መድኅን ከእናታቸው ወ/ሮ ዘገየሽ ደስታ በ፲፱፻፵ ዓ·ም በበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ ልዩ ስሙ ቁት አቡነ አረጋዊ ከተባለ ደብር ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር እንዳሉ ከአጐታቸው ቆሞስ አባ ምትኩ ገብረ መድኅን ፊደል ቆጥረው ንባብና ዳዊት ተማሩ ከዚያም ቀጥለው ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ያስተምሩ ከነበሩት ከአባታቸው ታላቅ ወንድም መሪጌታ ወርቁ ገብረ መድኅን ጾዋትወ ዜማ በሚገባ ተምረዋል ፡

መሪጌታ ፍሥሐ ከዚያ በመቀጠል ታላቅ ወንድማቸው መሪጌታ ውብአገኝ ባንተ ድጓና ዝማሬ ያስመረቁ ሊቅ ስለሆኑ ከእርሳቸው ድጓና ዝማሬ መዋሥዕት ከተማሩ በኋላ ወደ መካነ ኢየሱስ በመሄድ ስመ ጥር ከነበሩት መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ቅኔ ከእነ አገባቡ አጠናቀው ተምረዋል ። ከዚያም ድንቁሳ ቅ/ጊዮርጊስ ወደሚባለው ደብር ሄደው ከመሪጌታ ወልደሰማዕት ዓለሙ አቋቋም ተምረው ከማስተማር ደረጃ ደርሰው ነበር ።

መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ የመማር ፍላጐታቸው ገና ባለማክተሙ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብተው እስከ ፰ኛ ክፍል ከተማሩ በኋላ ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ት/ቤት በመዛወር እስከ ፲፪ኛ ክፍል ተምረው ሰርትፊኬት ተቀብለዋል ፡

ቀጥሎም ወደ ሥራ ዓለም ተሠማርተው በኢሉባቦር ሀ/ስብከት በቴፒ ከተማ የግል ጥናት ያካሒዱ ከነበሩ የውጭ ሀገር ዜጐች ጋር ሆነው በመዘዋወር የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተርጓሚ ሆነው ሠርተዋል ፡ በኋላም ባላቸው የትምህርት ችሎታ ላይ በመመሥረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጐት ስለነበራቸው በሐዋርያዊ ድርጅት ሥር ይተዳደር በነበረው በጎጃም ሀ/ስብከት በመተከል አውራጃ በወምበራ በቡለን ተቋቁሞ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ያስተምር በነበረው ት/ቤት ተመድበው ሲያስተምሩ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው መሆኑ ታውቆ በርእሰ መምህርነት በድሬክተርነት እንዲሠሩ ተደርጎ ትምህርት ቤቱን ለብዙ ጊዜ በአማረ ሁኔታ መርተዋል ፡ ትምህርት ቤቱ ወደ መንግሥት ሲዛወር በ፲፱፻፸፫ ዓ·ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በጠ/ቤተ ክህነት በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የትንሣኤ መጽሔትና የድምፀ ተዋሕዶ አዘጋጅ በመሆን በቅንነት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል፡



መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ እኒህ ነበሩ

መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ የ፫ ልጆች አባት ነበሩ መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ ትልቅ ትንሽ ሳይሉ ሁሉንም የሚያከብሩ ከሥራ ጓደኞቻቸውም ጋር ተግባብተውና ተመካክረው ከመሥራታቸውም ሌላ ጓደኞቻቸውን በመምከር ሲያዝኑና ሲበሳጩም በማረጋጋት የሚያደርጉት መንፈሳዊ ተግባር ከፍ ያለ ነበር ፡ በስብከት አሰጣጣቸውም ተናግረው የማይሰለቹ ነበሩ ፡ ዳሩ ግን ምንም ደግ ሥራ ቢሠሩ ሞት ለማንኛውም ሰው የማይቀር የተፈጥሮ ግዴታ በመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ “በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና የምሄድበት ጊዜ ደርሷል መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል



www.ethiopianorthodox.org

ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም" ብሎ እንደተናገረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እንዲኖሩ የፈቀደላቸውን ዘመን ፈጽመው በተወለዱ በ፸፩ ዓመታቸው በድንገት አደጋ የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ. ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ፡

የካቲት ፳፱ ቀን ከንጋቱ ፩ ሰዓት ጀምሮ የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ካህናት ለሊቃውንት የሚገባውን ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱላቸው ከዋሉ በኋላ የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በ፱ ሰዓት በቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞአል በቀብሩም ላይ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ብፁዕ አቡነ ቶማስ ብፁዕ አቡነ በርናባስ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የጠ/ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም የሥራ ጓደኞቻቸውና ወዳጆቻቸው ጐረቤቶቻቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን ተገኝተው ነበር ፡

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ኃላፊ ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሣን የሟቹን የሕይወት ታሪክ ካነበቡ በኋላ ባደረጉት ንግግር በመሠረቱ አባት በሥራ ሲደክም ውሎ ማታ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለስ ከቤት ወጣ ብለው የሚቀበሉት ልጆች ነበሩ መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ ግን ከሥራ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የተቀበላቸው ሞት ሆነ ። ሰው ብዙ ቀን ታሞ ቢሞትም እንደ መሪጌታ ፍሥሐ በድንገት ቢሞትም ያው ነው ሥጋ ለለበሰ ሁሉ የማይቀር ጉዳይ ነውና እኔና መሪ ጌታ ፍሥሐ ቅዳሜ ዕለት የተሰነባበትነው ሰኞ እንደምንገናኝ ነበር ነገር ግን የሰው አሳብና የእግዚአብሔር አሳብ የማይገናኝ በመሆኑ ትናንት ማታ ድንገተኛ ጥሪ መጥቶባቸው ተለይተውናል ፡ እንግዲህ ወዲህ እኛ ወደ እርሳቸው እንሄዳለን እንጂ እርሳቸው ወደ እኛ ይመጣሉ ተብለው አይጠረጠሩም እንግዲህ ሁላችንም የምንገናኘው በትንሣኤ ዘጉባኤ ስለሆነ የመጨረሻ ስንብታችን በኃዘን እየገለጽን ለቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትን ለነፍሳቸው ዕረፍተ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጥልን ዘንድ ቸሩ ፈጣሪያችን እንለምነዋለን በማለት ሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሣን ካሣ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ በርናባስ የአዲስ አበባ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ባስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ሞት በፈለገው መንገድ ቢመጣም ለሁሉ የማይቀር ዕዳ ነው እኛን የሚያስደነግጠን ሁልጊዜ በተለመደ መንገድ ባለመምጣቱ ብቻ ነው ለሞት ዋና መድኃኒቱ ሃይማኖትን አጽንቶ ሥነ ምግባርን አሳምሮ ተዘጋጅቶ መኖር ነው ምንም ወንድማችን መሪጌታ ፍሥሐ ባንተ ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ልጅ በመሆናቸው ዝግጅት አላደረጉም ባይባሉም እንደዚህ ያለው ድንገተኛ የሞት አመጣጥ ሁሉጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ ማንኛውም ክርስቲያን በሚገባ ተዘጋጅቶ ዕለተ ሞቱን መጠበቅ አለበት የዛሬውም የወንድማችን በሞት መለየት የሚያሳስበን ይህንን ስለሆነ ሁሉም ተዘጋጅቶ መኖር ይገባዋል ካሉ በኋላ ብፁዕ አቡነ በርናባስ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ሲፈጽሙ ኀዘንተኛው ከሟች ቤተሰቦች እየተሰናበተ ወደየቤቱ ሄዷል ። በወጣትነትም ሆነ በዕርጅና በድንገትም ሆነ ብዙ ቀን ታሞ በአልጋ ላይ እንደትኋን ተጣብቆ ኖሮ ቢሞት ሞት የማይቀር ዕዳ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከእኛ አንድ ስንኳን ለራሱ የሚኖር የለም ለራሱም የሚሞት የለም በሕይወት ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን" ብሎ እንዳስተማረን በሕይወተ ሥጋ የምንኖረው እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለመ ሥጋ ነው በሞት ብንለይም በነፍሳችን ሕያዋን ሆነን የምንኖረው እግዚአብሔር አምላክ ባዘጋጀት መንግሥተ ሰማያት ነው ። ነገር ግን በዚህ ዓለም ለተወሰነ ዘመን በምንቆይበት ጊዜ ከሕገ እግዚአብሔር ወጥተን ክፉ ሥራ ብንሠራ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀን እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋ መከነ ሥቃይ ነው ሁሉም አዘውትሮ መጸለይ የሚገባው ወደ ጥፋት አታግባኝ በእጄ ሠርቼ በልቤ አስቤ በቃሌ ተናግሬ አንተን አምላኬን እንዳልበድል ጠብቀኝ እያለ ነው ።

መሪጌታ ፍሥሐ ባንተም ምንም በአልጠረጠሩት ሰዓት ባላሰቡት ዕለት ድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው ቃለ ወንጌልንም በመማርና በማስተማር የኖሩ ሃይማኖታቸውን አጽንተው ሥነ ምግባራቸውን አሳምረው ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋርም በፍቅርና በመግባባት የሠሩ በመሆናቸው ቸሩ ፈጣሪ በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ ቃል ኪዳን በምትወረስ በመንግሥተ ሰማያት ነፍሳቸውን እንዲያሳርፋት ወደ ፈጣሪ እንጸልያለን ። ከትንሣኤ መጽሔት

ቀ.ሊ.ኅ. ልሣነ ወርቅ በዛብኅ



# በተመረጠች ቀን እሰማሃለሁ

ድኅነት በሚደረግባትም ቀን እረዳሀለሁ እነሆ የተመረጠች ቀን ዛሬ ናት የመዳንም ቀን ዛሬ ናት ፪ኛ ቆሮ. ፮ ፡ ፪ በዘመነ ኦሪት እስራኤል ከግብፅ የወጡባት ቀን የተመረጠች ቀን ትባላለች ።

ምክንያቱም እስራኤላውያን ለብዙ ዘመናት በግብፅ ለነበሩ ባለሥልጣኖች የጭቆና አገዛዝ ያለውድ በግድ ሲገዙና ሲሰቃዩ ኖረዋል ። ወንዶች ልጆቻቸውም ተዋግተው ከጠላቶቻቸው እጅ ነፃ እንዳያወጡዋቸው በሚወለዱበት ጊዜ በንጉሡ ትእዛዝ ወደባሕር እየተጣሉ አልቀዋል ።

በዚህ ጊዜ በጭቆና በትር ስለተደበደቡ እንደ ሕፃን ልጅ እያለቀሱ ወደአምላካቸው ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ጩኸታቸውን አሰሙ እግዚአብሔርም ለፍጥረቱ አዛኝ ነውና ጩኸታቸውን ሰምቶ እንባቸውን ተመልክቶ ሙሴንና አሮንን ልኮ ልዩ ልዩ ተአምራትን እያደረገ የግብፃውያንን የአገዛዝ ቀንበር ሠብሮ ነፃ አወጣቸው እነሱም የአምላካቸውን ኃይል አውቀው መሥዋዕት ሠውተው በዓሉን አክብረው የወጡባት ቀን የተመረጠች መሆንዋን አውቀዋል በዚህ ዓይነት ሰው ሁሉ ነፃነት የተጎናፀፈባትን ቀን የተመረጠች ናት ይላታል ይህ ነፃነት በሥጋዊው በኩል የሚገኝ ነው ።

፩ኛ/ የተመረጠች ቀን የተባለች በዘመነ ሐዲስ አንደኛ መጋቢት ፳፱ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተጸነሰባት ቀን ናት ።

፪ኛ/ ታኅሣሥ ፳፱ የተወለደባት እንዲሁም መጋቢት ፳፯ ቀን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶ ዓለምን ያዳነባት ዕለተ ዓርብ ፬ኛ መጋቢት ፳፱ ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት (የተመረጠች) ናት እንዲህም ስንል የጥንቱን መናገር ነው እንጂ የዛሬው በድሜጥሮስ አቆጣጠር ይወጣል ይወርዳል ። ይሁን እንጂ የዓለም ፈጣሪ የማዳን ሥራውን ሠርቶ የፈጸመባቸው ቀኖች ሁሉ የተመረጡ ናቸው ስለሆነም በነዚህ ቀኖች ክርስቲያኖች የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምንና የልጇን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓላት እንዲያከብሩ ሐዋርያት በሲኖዶስ አዝዘዋል ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ግበሩ በዓለ ለእመብርሃን በዘዜነዋ መልአክ ብለዋል ልበ አምላክ ዳዊትም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ሲናገር ጌታ እግዚአብሰሔር ለእኛ ተገለጸልን በዓልን በደስታ አክብሩ በማለት አስቀድሞ ተናግሯል ይህንንም ጊዜ ሲደርስ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ሆኖ በሥጋ የታየ እርሱ ነው በመንፈስ ቅዱስም የታወቀው እርሱው ለመላእክትም ታያቸው ለዚህም ማስረጃ ጌታ በተወለደ ጊዜ ለመላእክት ታይቷቸዋል ። እነርሱም ለእረኞች ነገሩዋቸዋል ። እረኞቹም ለሕዝቡ ተናግረዋል ።

፪ኛም በተነሣ ጊዜ እንዲሁ መጀመሪያ ለመላእክት ታያቸው እነሱም ለሴቶች ሴቶችም ለሐዋርያት ሐዋርያትም ለሕዝብ አስተምረዋል። ከዚህ በኋላ በዓለም ሁሉ ታመነ ወደሰማይ በክብር ዐረገ በዚህ ጊዜም በሁሉ ዘንድ በይበልጥ ታመነ በማለት የዳዊት ትንቢት መፈጸሙን ተናግሮአል ። ከዚህ ላይ የምናገኘው ፍሬ ነገር እኛም የጌታን በዓል በደስታ እናከብር ዘንድ ነው ። ፩ኛ ጢሞ. ፫ ፡ ፲፮ ሐዋርያው ጳውሎስ የተመረጠች ቀን ዛሬ ናት ያለው ግን ዘመነ ሥጋዌን ነው ወይንም መዋዕለ ንስሐን ነው ። ምክንያቱም በዘመነ ሥጋዌ የተሠራች ሕገ ወንጌል አብዛኛውን ጊዜ የምትሰብከው ስለይቅርታና ስለ ምሕረት እንዲሁም ስለንስሐ በመሆኑ ነው ። ከዚያ በፊት በነበረችው በዘመነ ኦሪት ግን አንድ ሰው ኃጢአት ቢሠራ በደንጊያ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሞት ነበር እንጂ ምሕረትና ይቅርታ አይደረግለትም የንስሐ ቀንም አይሠጠውም ነበር በወንጌል ግን ይህ ሁሉ ቀርቷል።

እንግዲህ ከርእሱ እንደተገለጠው የተመረጡ ዕለታት ለመልካም ሥራ የተዘጋጁ ቢሆኑም ሰው ሁሉ ቃለ ወንጌልን ተምሮ የቀረውን ሃይማኖት አውቆ መልካም ሥራን ሠርቶ ንስሐ ገብቶ ከፈጣሪው ጋር ታርቆ ገነት መንግሥተ ሰማያትን ሊወርስ ካልቻለ የቀኖቹ መመረጥ ምን ይጠቅመዋል።

ይህን ያወቁ ብልሆች ሰዎች ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ዘመን አብዝቶ ወራት አስፍቶ መስጠቱ ሰውን ሁሉ ለንስሐ ሊያስገዛው እንደሆነ በመረዳት ፈጥነው ንስሐ ገብተው ከሚመጣው ሥቃይ ይድኑበታል ፤ አሁንም ቢሆን በተመረጠች ቀን እሰማሃለሁ ቢልም ሰነፍ ሰው ጸሎቱን እንደሚሰማው ሰማኝ ብሎ አይለምነውም እንዳይረዳውም እርዳኝ አይለውም ወይም ለንስሐ ሞት አብቃኝ እያሊ አይጸልይም ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## የርእሰ ደብር አበበ ጅሩ የሕይወት ታሪክበአጭሩ

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ ከአቶ ጅሩና ከወ/ሮ ወለተ ጊዮርጊስ ብርቄ በ፲፱፻፫ ዓ·ም በሰላሌ አውራጃ በግራና ጃርሶ ወረዳ ሸንኩርት ደብረ ፍሥሐ ቅ/ሚካኤል አካባቢ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ መምህር ገብረ ሥላሴ ከተባሉት **መምህር ፊደል ቆጥረው** ንባብ በማንበብ ዳዊት ደግመው ጸዋትወ ዜማም በሚገባ ተምረዋል በ፲፱፻፲፰ ዓ·ም በተወለዱ በ፲፭ ዓመታቸው ወደጎጃም ክፍለ ሀገር በመሄድ የሩዝ ከተባለው ደብር ስመ ጥሩ ከነበሩት አለቃ ልሳነ ወርቅ ቅኔ ከእነ አገባቡ ተምረው ለመምህርነት ከሚያበቃ ዕውቀት ደርሰዋል ።

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ የትምህርት መቀበል ተሰጥዎ ስለነበራቸው ከዚያ ወደብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ በመሄድ ከታላቁና ከገነኛው መምህር አለቃ ውብሸት ዘንድ የቅኔ ትምህርታቸውን አስፋፍተው በመማር በመምህርነት ተመርቀዋል ከእኒሁ መምህር የመጻሕፈ ነገሥት ትርጓሜን ቀጥለዋል ሁለተኛም መጀመሪያ ቅኔ ወደተቀኙበት ወደሩዝ ተመልሰው ከአ

ሊቃ ልሣነ ወርቅ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜን ቀጽለዋል ። አቡሻክርም ጨምረው ተምረዋል ።

በ፲፱፻፳፬ ዓ·ም በተወለዱ በ፳፩ ዓመታቸው ወደትውልድ ሀገራቸው ሰላሌ ተመልሰው ዳግማሚ ተሰማ ዱባለ ከተባሉት መምህር **ጾመ ድጓና መዋሥዕትና ዝማሬ አቋቋምና ቅዳሴ በሚገባ ተምረው ለማስተማር ተመርቀዋል ።**



ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ እኒህ ነበሩ

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ በተለይ በቅኔ ትምህርት ከፍተኛ ዕውቀት ስለነበራቸው በተቀኙ ጊዜ ሊቃውንቱ በጣም ያደንቁና ይደሰቱ ነበር ።

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ቅኔ ፀዋትወ ዜማ ቅዳሴ ሰዓታትና የቁሙ ጽሕፈት በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

፪ኛ ደብረ ፍሥሐ ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከታነፀ ብዙ ዘመን ስለሆነው በጣም ተጎሳቁሎና ለመፍረስ ተቃርቦ ስለነበር ምእመናኑን በማስተባበርና ራሳቸውም ከገንዘባቸው በማውጣት **ቤተክርስቲያኑ እንዲታደስና የተጓደለውም ንዋየ ቅድሳት እንዲሟላ አድርገዋል ።**

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ ርኅሩኅና ደግ ከመሆናቸው የተነሳ ማንኛውንም ችግረኛ ለመርዳት እጃቸውን ይዘረጉ ነበር የተራበ ማብላት የተጠማ ማጠጣት የታረዘ ማልበስ ከሚፈጽሟቸው ሥነ ምግባራት ጥቂቶች ነበሩ ።

### ጋብቻ

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ ወ/ሮ **ፀዳለ ጉርሙ የተባሉትን ሴት** በ፲፱፻፳፯ ዓ·ም በተክሊል አግብተው ፬ ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ ወልደዋል ስለሆነም ትውልደ ጻድቃን ይትባረኩ ክብር ወብዕል ውስተ ቤቱ (መዝ·፩፻፲፩) የጻድቃን የቅኖች ትውልድ ትባረካለች ክብርና ባለጠግነትም በቤቱ ነው ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት የርእሰ ደብር አበበም ልጆቻቸው የተባረኩና የተቀደሱ ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪዎች በመሆንና የአባታቸውንም መንፈሳዊ አሠረ ፍኖት በመከተል ላይ ይገኛሉ ።

ልጆቹ በጠቅላላ የወላጆቻቸውን መልካም ሥነ ምግባር የወረሱ በመሆናቸው ለቤተክርስቲያኑ ሕንፃ ማሳደሻ ገንዘብና ማቴሪያል ለመቀደሻ የሚሆኑ አልባሳትንና ንዋያተ ቅድሳትን እንዲሁም መጻሕፍትንና ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን በየጊዜው ይለግሳሉ ።

ርእሰ ደብር አበበ ጅሩ ከላይ እንደተጠቀሰው ወንበር ዘርግ**ተው ከሚያስተምሯቸው ትምህርቶች** በቤተ ክርስቲያን እሁድና

ይሁን እንጂ "ለተቀማጭ ሰማይ ቅርብ ነው" እንደሚባለው በሰው እንፈርዳለን እንጂ ሁላችንም ያውነን ።

፪ኛም ቁስ ካናዘዘው እድሜ የናዘዘው ይሻላል እድሜ ለንጉ[...]ሐ ዘመን ለፍስሐ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔርን መለመን ይገባናል። መ ደባቢ መልአክ



# "ሁሉ ተፈጸመ አለ"

በዚህ ኃይለ ቃል መነሻነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት መጀመሪያና ሁለት ፍጻሜ እናገኛለን ።

፩· በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ፣ ዘፍ ፩ ቁ

፩· በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፣ ያለው ሲሆን ሁለት ፍጻሜ የተባለው ደግሞ የሰማይና የምድር መፈጠር የፍጥረት መጀመሪያ እንደሆነ መጨረሻውም ፮ኛው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል" እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ ሁሉ በ፮ኛው ቀን ፈጸመ በሰባተኛው ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ አረፈ ሰማይና ምድር ሥራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ ብሎአል ዘፍ ፪ቁ· ፪ ።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ያለው ከዓለም መፈጠር በፊት የነበረው የእግዚአብሔር አብ አካላዊ ቃሉ በረኸርም እቅዱ ተይዞ የነበረውን የሰውን ልጅ መዳን መሠረት መጣሉን ያሳያል ። መሠረት "ቃል ሥጋ ኾነ" ዮሐ ፩ቁ ፲፬" የተባለው ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል መወለዱ ነው ። ይህውም (የዘመኑ ፍጻሜ) በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ ባለው ይታወቃል ገላ ፬ቁ ፬"

እንግዲህ የጌታችን ልደት የመዳናችን መሠረት ከሆነ ፣ መደምደሚያ ፍጻሜው ስቅለቱና ትንሣኤው መሆኑን እንረዳለን ። "እስመ በመስቀሉ አምላክ ፈጸመ መድኃኒተ" አምላክ በመስቀል ላይ በመሰቀሉ ድኅነተ ፈጸመ ተብሎ ተጽፎአልና ። እንቀጸ ጸሎት ፍትሕ መንፈሳዊ ፲፬ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ያከናወናቸው ተግባሮች ሁሉ በአፈጻጸማቸው ብቻ ያለ አንዳች ሰባኪ ሰውን የሚያሳምኑ ናቸው ለምሳሌ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን በዐይኑ ልቡና ብንመለከተው ለመሆኑ በድንግልና ተፀንሶ (ተረግዞ) በድንግልና የተወለደ ሥጋ ለባሽ ማንንው? በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ዘፍ ፲፰ ቁ ፲፰ ተብሎ ተስፋ ትንቢት ከተሠጠው ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ በየጊዜው ከተነሡ ነቢያትና ሐዋርያት ጻድቃንና ሰማዕታት በድንግልና የመወለድ እድል ያገኘ አሉን ተብሎ ቢጠ**የቅ መልሱ የሉም ይሆናል ። ምክንያቱም የአወላለዳቸው** ቅያስ ብዙ ተባዙ በተባለው ማባዣ መሥመር የተቀየሰ በመሆኑ ነው። ምንም እንኳ ሰመልከጼዴቅ አባትና እናት የለውም ብሎ ሐዋርያው ቢጽፍለትም ቅሉ፡ በአሪት ዘሌዋውያን ስለአል ተጻፈ ነው በማለት መምህራን የክርክሩን በር ዘግተውታል ።

የጌታችን ልደቱ ግን ከአባት ብቻ ያለ እናት ከእናት ብቻ ያለ አባት በመወለዱ አፈጻጸሙ ብቻ (መምህር ሆኖ) ፍጹም አምላክም ፍጹም ሰውም መሆኑን ያሳምናል" ያም ባይሆን በሥራዬ እመኑኝ ያለው ስለዚህ ነው" ዮሐ ፲፬ ·ቁ ፲፩

የትንሣኤውም ሁኔታ እንዲሁ ሌላ አስነሽ ምክንያት ሳይኖረው በአምላካዊ ሥልጣኑ የተፈጸመ ነው ።

እነሆ ከአባታችን ከአዳም የወረስናቸው ፭ ነገሮች ነበሩ ። እነርሱም ፣ ሀ/ ሞት ለ/ወደ መቃብር መውረድ ፣ ሐ/መፍረስ አፈር ትቢያ መሆን ፣ መ/የማኅፀን ቁራኛነት ሠ/ የሲኦል ቁራኛነት ናቸው ለምሳሉ እግዚአብሔር **ወልድ ያለ ምክንያት ያለ ዘር**

ከቤተሰቦቻቸው



www.ethiopianorthodox.org

ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ተውህዶ በእመቤታችን ማኅፀን በማደሩ ዘርዐ ብእሲን ምክንያት በማድረግ ፅንስን በማኅፀን ይቆራኝ የነበረውን የዲያብሎስን ቁራኝነት አጥፍቶልናል ጌታ የተፀነሰው እን በለዘር፣ የተወለደውም ያለ ዘር ነውና። ፱/በሞት ጊዜ የሰውን ነፍስ አስከፊ መልኩን በማሳየት አስደንግጦ ከሥጋዋ ለይቶ በመቆራኘት ወደ ሲኦል ያወርዳት ነበር።

ጌታ ግን ይህን ችግር ለማስቀረት ሲል አባት ሆይ ነፍሴን ላንተ አደራ እሠጣለሁ ማቴ ፳፯ ቁ ፶ ማር ፲፭ ቁ ፴፯ ሉቃ ፳፫ ቁ ፵፮ በማለት ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በመለየቱ በኩር ሆኖን በመዓዛ ገነት ፣ በእደ እግዚ አብሔር ነፍሳችን ከሥጋችን እንደት ለይ አድርጎልናል ።

፲/ በመቃብር ፈርሰን አፈር ሆነን እንቀር የነበርነውን የተፈጥሮ ልማድ ለውጦ ሙሉ አካል አግኝቶን በትንሣኤ ታድሰን እንድንነሣ አድረጎናል ፩ኛ ቆሮ ፲፭ቁ ፵፱ — ፶፬ በመበስበስ ይዘራል ባለመበስብስ ይነሣል ፣ በድካም ይዘራል በኃይል ይነሣል ።

፲፩ኛ/ በሰይጣን ሥልጣን ተገድደን ወደ ሲኦል እንወርድ የነበረውን አስቀርቶ በሲኦል ያላችሁ ውጡ በጨለማ ያላችሁ ተገለጡ ብሎ በአዋጅ ነፃነትን ስለሠጠን ፣ የትንሣኤና የዕርገት በኩራችንን እርሱን ተከትለን እርሱ ከገባበት ውሣጤ መንጦላዕት እንድንገባ እድል ሠጥቶናል ።

"አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ የሰጠ ሸኸኝን ክብሬን እንዲያቁ እነርሱ ደግሞ እኔ ባለሁበት ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ" ዮሐ ፲፯ ቁ-፳፬ በዚህ ዓይ

## የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ መዓዛ አስማማው

# ሴቶች ትንሣኤውን ሰበኩ

"ማን ያውራ የነበር ማንያርዳ የቀበር" ሲሉ አበው እንደሚ መስሉት ድርጊቱ ሲፈጽም የነበሩ ሴቶች ትንሣኤውን ለመስበክና ለመናገር ዕድል አግኝተዋል። በመሠረቱ ሴቶች ትንሣኤውን ለመስበክ የበቁት ያለምንም ችግር አልነበረም ። ብዙ ስቃይ ደርሶባቸዋል ፍርሃትና ድንጋጤ ከብቦአቸዋል የመቃብሩን ድንጋይ ማን ያንከባልልናል ብለው በሐሳብ ተጨንቀዋል በተነሳበት

ዕለት የክርስቶስን ሥጋ ሽቶ ሊቀቡ ወደ መቃብርም ሄደዋል ክርስቶስ ከተያዘበት ሌሊት ጀምሮ ፈርተው አዝነውና ተስፋ ቆርጠው የሚነጋገሩት ስለዚሁ ሁኔታ ነበር ።

የዘኑበትም ዋናው ምክንያት

ነት ከጊዜ ፅንስ እስከ ጊዜ ሞት የነበረብንን ፍዳ ነቀል አድርጎ አዳነን የተባለው ስለዚህ ነው ። እንግዲህ ባለፈው ስሕተታችን የመጣብንን ዕዳ ሰው ወዳጅ የሆነው አምላካችን እኛን ሆኖ ዕዳችንን ከፍሎ አድኖናል ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደ ሥራችን መጠን ዋጋ ሊከፍል ይመጣል እንጂ ፪ኛ ሊሰቀልና ሊሞትልን አይመጣ ምና ወደ ክፉ ሥራ ከማዘንበል ፈጣሪያችንን ከመበደል እንጠንቀቅ ። አጥብቀንም እንራቅ "ዕብ-፮ ቁ-፮"

በየአደባባዩና በየሥፍራው እየተዘዋወረ የሚመክር የሚያስተምር የሚፈውስ የነበረው መምህራቸው ክርስቶስ ንፁህ መሆኑ እየታወቀ ወንበደውን በርባንን ፈትተው እሱን ግን እንደጥፋተኛ ቆጥረው በአይሁድ ሊቃነ ካህናትና በመሰሎቻቸው የሐሰት ፍርድ ተፈርዶበት ከሕግ ውጪ በመሰቀሉና በመሞቱ ነው ።

በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ጌታና አምላክ ሆኖ ሳለ ወደ መቃብር ሲወስዱት እንደ ደሃ አስከሬን ሳይታጀብ ከመስቀሉ አውርደው ጥቂቶች ሰዎች አስከሬኑን አንስተው ለሌላ ሰው በተሠራ መቃብር ውስጥ ሲቀብሩት በማየታቸው ሐዘናቸው የጸና (የበረታ ሆነ ፡

በዚህ ጊዜ እንባቸውን ከማፍሰስ ከማዘንና ከመጨነቅ ባያቋርጡም እንኳን የዚህ ህግ ሻሪ መምህር ተከታዮችና ግብረአበሮች ተብለን ተይዘን እንታሠራለን ብለው ሳይፈሩ ሐዘናቸውን በሰው ፊት ከመግለጥ ያገዳቸው ኃይል አልተገኘም ።

ምንም እንኳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክስ እስቲ ራስህን አድን "እያሉ ያፌዙበት የነበሩት ጠላቶቹ" ይኸውላችሁ የእናንተ ጌታ መወረሻው እስከዚህ ድረስ ነው እያሉ" ቢያሳጧቸውም ከአንጻረ መስቀሉ ፊት ለፊት ቆመው የመ



ከራው ተካፋይ መሆናቸውን አላቋረጡም ።

ይሁንና ጠላቶቹ የድፍረት ቃል እየተናገሩ ቢያሾሚጥጡም የሕይወት ባለቤት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አላንቀላፋም ጠላቶቹን የሚያሳፍር በታላቢዎች ዘንድ አድናቆትን የሚያተርፍ ተከታዮችን የሚያጽናና እና የሚያረጋጋ ተአምር ይሠራ ነበር ቅዱስ ሥጋው በመቃብር ቢያርፍም መለኮት በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ለታሠሩና ለተጋዙ ለኃጢአት እሥረኞች ነፃነትን ሰብኳል ። ፩ኛ ጴጥ.፫—፲፱ ከዚህም ሌላ ወንጌላዊው ማርቆስ በም ፲፮ቁ.፩-፰ የትንሣኤውን ተአምር የእነርሱን ሥራ ገልጾታል ። ወደ መቃብር የሄዱትን ማርያም መግደላዊት የያእቆብ እናት ማርያም እንዲሁም ሰሎሜ በአራቱ ልማድ የጌታችንን ሥጋ ሽቱ ሊቀቡ ሄዱ እንጂ ተአምር እናያለን ብለው በጭራሽ አላቀዱም ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም በሥልጣኑ ሞትን ድል ነስቶ እናገኘዋለን የሚልም ግምት አልነበራቸውም። ይሁን እንጂ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ያላሰቡትንና ያልገመቱትን መልካም ዜና ለመስማት አበቃቸው በመቃብሩ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ የሚከተለውን የምሥራች ነገራቸው አትደንግጡ የተሰቀለውን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቷል በዚህ የለም።ሄዳችሁ ለደቀመዛሙርቱ ወደገሊላ ይቀድማችኋል ብሎ እንደነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሯቸው ሲል መልካም ዜና ነግሯቸው እየተደሰቱ ሄዱ ።

ከዚህ ቀደም ማለትም በአራቱ ጊዜ ሴቶች እንዳያስተምሩ የአይሁድ ካህናት ተጽዕኖ ያደርጉባቸው ነበር።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማር ከጀመረ በኋላ ግን ከሐዋርያት ጋር የክርሱ ተካፋይ ሆነው ከመሰልጠናቸውም በላይ ክርስቶስ በተነሣበት ዕለት የእግዚአብሔር መልአክ ትንሣኤውን ነግሯቸው ሰብከውና አስተምረው ለብዙ ሰዎች መስክረዋል ይህም ለሴቶች ታላቅ የምሥራች ነው ። ከጌታችንም ዕርገት በኋላ በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ፴፮ቱ ቅዱሳት አንስት አልተለዩም በጸሎት በማዘዝና በመታዘዝ ይተባበሩ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል በቁጥርም ከወንዶቹ ይበልጡ ነበር ።

በጊዜው የተሠራው መልካም ሥራ በየጊዜው ለተነሱት ሴቶች የሥራ ምዕራፍ እንደሚከፍት አያጠራጥርም ቤተ ክርስቲያናችን እስከ ዛሬ ድረስ ፊደል አስቆጥራ ከተራ እስከ ዶክተር ያደረሰቻቸው ሴቶች ኧረ የትገብተው ይሆን ምን ተዕእኖ ይዟቸው ይሆን? ወይስ ስለ እግዚአብሔር መናገር አልፈለጉም ? ለምን ?

በእርግጥ መመስከር መድረክ ላይ ቆሞ ወይም ሕዝብ በአደባባይ በተሰበሰበበት ቦታ ብቻ አይደለም በልዩ ልዩ ዘዴና ጥበብ ስለእግዚአብሔር መመስከር ይቻላል ። በይበልጥም ብእርና ወረቀትን በማገናኘት ። ታዲያ ሴቶች የታጠፈው እጃችሁ ተዘርግቶ መንፈሳዊ ሥነ ጽሑፎችን በትንሣኤ መጽሔት የሴቶች ዓምድ ብታቀርቡ ዓምዳችን በትህትና ተቀብሎ ያስተናግዳል ።

ወደ ተነሣንበት ታሪክ መለስ ስንል ጌታችን የመጣበትን ዓላማ እንደፈጸመ ይገልጽልናል የክርስቶስ ተከታዮች ያዘኑት የተሸበሩትና ተስፋ የቆረጡት ጌታቸው ያለአግባብ ተከሶ የሚያስቅቅ ሞት ስለደረሰበት ነው እንል ይሆናል። ይህ ሁሉ ሲደርስባቸው የቻለው ፫ ዓመት ሙሉ እያዘለሁ እሰቅላለሁ እሞታለሁ በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ እያለ ለእነርሱና ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸውንና ያስተማራቸውን በመርሳታቸው በተጨማሪም ዓለምን ለማዳን ሰይጣንን ድል ለመንሳትና ሞትን ለማሸነፍ መምጣቱን በመዘንጋታቸው መሆኑን ልናስታውስ ይገባናል ።

እንግዲህ ለሴቶች አትደንግጡ ተነሥቶአል ሲል በመልአኩ የተነገረው ቃል በኃጢአት የቆሰለውን የእያንዳንዳችንን ሕይወት ይፈውሳል በሐዘን የተሰበረውንም ልባችንን ይጠግናል ተስፋ የቆረጠውንም ልብ በአዲስ ተስፋ ይቀሰቅሳል ።

በዚህ አንጻር የትንሣኤው ቃል ለእያንዳንዳችን የተስፋና የአዲስ ሕይወት የምሥራች ሊሆን ይገባል የረሱት ሴቶቹ ብቻ ሣይሆኑ ሁላችንም አምላካችን በየጊዜው የዋለልንን ውለታ እንረሳለን ከዚህ በፊት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ሰምተን በሙሉ እምነት እርሱን ለመከተል የጀመርንበት ጊዜ ነበር ።

እምነታችንና ምግባራችን አፍላ በሆነበት ጊዜ ደስታም ሐዘንም ክብርም ውርደትም ሀብትም ድህነትም እግዚያብሔርን እንድናስብ ይቀሰቅሱን ነበር። አሁን ግን ብዙዎቻችን ሰይጣን የተንኮል መረቡን ዘርግቶ በኃጢአት ወጥመድ በየጊዜው እንዳያስረን



www.ethiopianorthodox.org

# የመልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው አጭር የሕይወት ታሪክ

መልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው በወሎ ሀ/ስ ዋድላ ደላንታ አውራጃ ልዩ ስሙ ጉልት ማርያም በተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከደብተራ ላቀው የተመኘ ከእናታቸው ከወ/ሮ ድንቅነሽ ወርቁ መስከረም ፳፯ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በተወለዱበት በጉልት ማርያም ከመሪጌታ እሸቴ ከፊደል ቆጠራ እስከ ንባብ ፡ ዳዊትና የቃል ትምህርት ተማሩ ፡

ከዚያም በዕድሜ እያደጉ በትምህርት እየበሰሉ ሲሄዱ ዋድላ በሚገኘው የነጃ ሚካኤል የቅኔ መምህር ከነበሩት ከአለቃ ደሴ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀኙ ። ቀጥሎም የቅኔ ትምህርታቸውን ለማሻሻል ደላንታ በጉድባ ቅ ጊዮርጊስ የምርምር ቅኔ መምህር ከነበሩት ከአለቃ ብሩ የምርምር ቅኔ ተቀኙ ። እንደገና የቅኔ ትምህርታቸውን በይበልጥ ለማጠናከር ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ዋድላ ተመልሰው በአብዲቆም ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰምና ወርቅ ቅኔ መምህር ከነበሩት ከአለቃ ይትባረክ ሰምና ወርቅ ቅኔ በሚገባ ተምረው አጠናቀቁ ።

ከዚህ በኋላ በመቄት ገረገራ ቅ/ጊዮርጊስ የድጓ መምህር ከነበሩት ከአለቃ መንግሥቱ ጉሹ ዳዊት ዜማና ድጓ ተማሩ ።

እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ደላንታ በመመለስ በሰለና ማርያም የተክሌ አቋቋም መምህር ከነበሩት ከአለቃ ቦጋለ የተክሌ አቋቋምና ዝማሬ መዋስዕት አጠናቀው ተምረው ጨርሰዋል ።



መልአከ ስብሐት ታረቀኝ እኚህ ነበሩ

በጠቅላላ በመንፈሳዊ ትምህርት ዓለም ውስጥ ለ፳ ዓመታት ቆይታ ካደረጉ በኋላ ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ወደ ትውልድ ቀበሌያቸው ወደ ጉልት ማርያም ተመልሰው እስከ ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. ለሶስት ዓመታት ያህል የጊገራ ሚካኤል መሪጌታ በመሆን ክርስቶስ በደሙ የዋጃት ቅ/ቤተ ክርስቲያንን በጥዑም ልሳን ልብን በሚመስጥ ጣዕመ ዜማ በቅንነት እያገለገሉ በአካባቢ የሚገኙትንም ምእመናን እያስተማሩ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም መጨረሻ ከትውልድ ቀያቸው ተነስተው ወደ ኩሎ አውራጃ መጡ ።

ከዚያም የዋካ ቅ/ጊዮርጊስ እና የዋካ ኢየሱስ መሪጌታ ሆነው እንዲያገለግሉና የአካባቢውን ሕፃናትም እንዲያስተምሩ ከ፲፱፻፴፩—፲፱፻፵፫ ዓ.ም. ድረስ በኩሎ አውራጃ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩ በመንፈሳዊ አገልግሎት ለ፲፪ ዓመት ያህል ሲያገለግሉ ቆይተው ከ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ ከኩሎ አውራጃ ወደ ከፋ አውራጃ ተዛውረው በመምጣት በከፋ አውራጃ የግራዊ ቅ/ጊዮርጊስ መሪጌታና የአካባቢው ሕፃናት መምህር ሆነው ተመደቡ ። በዚሁ መንፈሳዊ ሥራቸው ያለ ማቋረጥ በመቀጠል በከፋ አውራጃ በጠሎ ወረዳ በዋሽ ቅ/ሚካኤል የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን እየተዘዋወሩና በጠሎ ወረዳ በዋሽ ቅ ሚካኤል ለ፲ ዓመታት ያህል አገልግለዋል ።

መልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው በከፋ አውራጃ ሳሉ በመንፈሳዊ ሥራቸው ዕውቀትን ከሥነ ምግባር ጋር አስተባብረው የያዙና የቅ/ቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት የነበሩት የግብጽ ተወላጅ አቡነ ቄርሎስ የተሠጣቸውን መንፈሳዊ ኃላፊነት የሥራ አደራ ዘንግተውና ወደ ጕን ትተው (ጥለው) በመሸሻቸው በምትካቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው ሊቃውንት መካከል ብቁ ሊቀ ጳጳስ መርጦ ለመሾም እንዲቻል በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ተደርጎ በነበረው መንፈሳዊ የሃይማኖት ጉባዔ ላይ እንዲገኙ የቀድሞው የከፋ ጠቅላይ ግዛት ሀገረ ስብከት ወክሎአቸው ስለነበር በውክልናቸው መሠረት አዲስ አበባ ሄደው ለሁለት ወራት ያህል በአማካሪነት ቢሠሩ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲሾሙ ሰምና ወርቅ ለበስ አዘል የሆነ ቅኔ አስተያየት ሰጥተው ጥቆማም አቅርበው ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ተቀብሎ በማድነቅ አጽድቆላቸዋል ።

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም ወደ እስክንድርያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሂደው የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ ሹመት ተቀብለው ተመልሰዋል ።

ከዚህ በኋላ በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም. የአለን ቅ/ጊዮርጊስ ጽላት ከከፋ ወደ ጅማ ሲመጣ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ አብረው በመምጣት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ ለ፵፱ ዓመታት ያህል የአለን ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መሪጌታና አለቃ ሆነው አገልግለዋል ።

በተጨማሪም ቀደም ሲል በሀገረ ስብከቱ መንፈሳዊ ት/ቤት በዕድሜ ብቁነት በጡረታ እስከ ተገለሉበት እስከ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ድረስ የአማርኛ ሰዋሰውና መንፈሳዊ መዝሙር መምህር ሆነው ሠርተዋል ። መልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው በ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. በብፁዕ ዶክተር አቡነ ጢሞቴዎስ መልካም ፈቃድ መልአከ ስብሐት ተብለው የማዕረግ ስም ተሰጥቷቸዋል ።

የአለን ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንና የአካባቢው ሕዝብ በዛሬው ቀን አንድ ታላቅ ሰው አጥተዋል ።

መልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው በሕይወት በነበሩበት ዘመናቸው ይታዩባቸው የነበሩ ዋና ዋና ገፀ ባሕሪያት ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ መልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው በሰምና ወርቅ የንግግር ለዛቸው በሰዎች ዘንድ እጅግ የሚመሰገኑ ምን ጊዜም የማይሰለቹ ነበሩ ።

፪ኛ/ በመንፈሳዊ ማህሌት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው ከፍ ያለ ፍቅርና ችሎታም ነበራቸው ።

፫ኛ/ ለሚጠይቃቸውና ለሚያነጋግሩአቸው ሰዎች ሁሉ በሰምና ወርቅ የተደገፈ መልስ መስጠት የሚችሉ ታላቅ ምሁር ነበሩ ።

፬ኛ/ በተቀደሰ አላማቸው በእግዚአብሔር ፍቅር የፀኑ

፭ኛ/ ሰውን ተናግረው የማያስቀይሙ

፮ኛ/ ቅን የዋህና ርህሩህ ነበሩ

፯ኛ/ መልአከ ስብሐት ታረቀኝ ላቀው ባለትዳርና የሁለት ሴቶች ልጆች አባት ነበሩ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ያገቡዋቸው የረጅም ጊዜ ባለቤታቸው ወ/ሮ ዘነበች ከበደ የገቢ ምንጫቸው በፈቀደው የገንዘብ መጠን ሊደረግላቸው የሚገባውን ሁሉ ሲያደርጉላቸውና ሲረዱዋቸው እንዲሁም ሲያስታምሟቸው ከቆዩ በኋላ ሞቶሙስ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ እንዳለው የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው በመሆኑና አዳም መሬት አንተ ወትገብዕ ውስተ መሬት ባለው መሠረት ዘሮ ዘሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከሞት አይቀርምና በተወለዱ በ፺ ዓመታቸው ጥር ፳ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ከቀኑ በአሥር ሰዓት ከ፲ ደቂቃ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ለ፵፱ ዓመታት ያህል ባገለገሉበት በአለን ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የቀብር ሥርዓታቸው ተፈጽሟል።

ሊቀ ካ. ብርሃ[illegible]

## ከቅዱስ መጽሐፍ ቃላት

“እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ ገንዘብን እንጀራ ላይደለ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው ጆሮአችሁን አዘንብሉ ፡ ወደ እኔም ቅረቡ ስሙ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች የ[illegible]ውን የዳዊትን ምሕረት፣ የዘለዓለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ።

እነሆ ለአሕዛብ ምስክር ለወገኖችም አለቃና አዛዥ እንዲሆን ሰጥቸዋለሁ እነሆ የማታውቀውን ሕዝብ ትጠራለህ የእስራኤልም ቅዱስ አክብሮሃልና ስለአምላክህ ስለ እግዚአብሔር የማያውቁህ ሕዝብ ወደ አንተ ይሮጣሉ ።

እግዚአብሔርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል ፡ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ”
ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ.፶፭:፩ ፯



www.ethiopianorthodox.org

# ጻድቁ አባ ገሪማ

አባ ገሪማ የትውልድ ሀገራቸው ሮም ነው የወላጅ አባታቸው ስም አስግንያኖስ እናታቸው ሰፍንግያ ትባላለች ወላጆቻቸው መካኖች ሆነው ልጅ ሳይወልዱ ብዙ ጊዜ ሲኖሩ ልጅ እንዲሰጣቸው ወደ ፈጣሪያቸው ይጸልዩ ነበር ።

የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ ጸሎታቸውን ሰምቶ ልጅ ሰጣቸው ስሙንም ይስሐቅ አሉት ደስታ ማለት ነው ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ትምህርት ቤት አስገቡትና እየተማረ አድጎ ሶማዕረገ ዲቁና በቅቶ ይቀድስ ጀመር ።

አባቱ አስግንያኖስ የሮም ንጉሥ ስለነበር እርሱ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ጊዜ መኳንንቱ መሳፍንቱ ሕዝቡም ተሰብስበው በአባቱ እግር ተተክቶ እንዲያስተዳድራቸው አነገሡት አባ ገሪማም በአባቱ ወንበር ነግሦ ፯ ዓመት እንደገዛ አባ ጰንጠሌዎን ደብዳቤ ላከለት የደብዳቤውም ቃል ልጄ ይስሐቅ ሆይ ሙታንን ተዋቸው በድናቸውን ይቅበሩ አንተ ግን የክርስቶስን መንግሥት ትወርስ ዘንድ ወደ እኔ ና" የሚል ነበር ።

**አባ ገሪማ ከአባ ጰንጠሌዎን የተላከለትን ደብዳቤ ካነበበ በኋላ ሳይውል ሳያድር ዕለቱን መንበረ መንግሥቱን ርግፍ አድርጎ ትቶ በሌሊት መነነ ወደ አባ ጰንጠሌዎን ሲጓዝ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል እየመራ አባ ጰንጠሌዎን ካሚኖርበት ቦታ አደረሰው ርቀቱ** [illegible] ት የሚያስጉዝ ነበር አባ [illegible] ኣት ሰዓት [illegible]

አባ ጰንጠሌንም በደስታ ተቀብሎ ሥርዓተ ምንኩስናን በሚገባ አስጠንቶ አመንኩሰው ዘመኑም በሀገራችን ኢትዮጵያ አልአሜዳ የነገሠበት ነበር አባ ገሪማ ከአባ ጰንጠሌዎን ተሰናብቶ ወደ መደራ ሄደ ሐውጼ የምትባለው ቦታ የምትገኘው ትግራይ ሀ ስብከት ስባት አውላሎ አውራጃ ነው ።

አባ ገሪማ አጋንንትን እያባረረና ከሰው እያወጣ ድውይ እየፈወሰ ፳፯ ዓመት ኑሯል ። ከሥራቸው ተአምራት ጥቂት እንጥቀስ፡ ከዕለታት አንድ ቀን ጧት ሥንዴ ዘርቶ ለሥርክ መሥዋዕት አድርሷል ሥንዴው የተወቃውም (የተበራየውም) ከመሬት ላይ ሳይሆን ከግራር ዛፍ ላይ ነበር ምርቱ (ፍሬው) ወደታች ሲወርድ ገለባው ተለይቶ ወደላይ ቀርቷል ምርቱም ፳፯ ዕንቅብ ሆነ ።

፪ኛ የወይን ሐረግ ከደንጊያ ላይ ተክሎ በማብቀል ለሥርክ መሥዋዕት አድርሷል ይላል መጽሐፈ ገድሉ መጽሐፍ ሲጽፍ የፈለገውን ጨርሶ ሳይጽፍ ፀሐይ ልትገባበት ስትል አውግዞ አቆመና ጽሕፈቱን ሲጨርስ ፀሐይን ከውግዘት ፈቶ ሥራዋን እንድትቀጥል አድርጓል ። አባ ገሪማ ምራቁን የተፋበት ደንጊያ አሁንም እንደፀበል እየፈለቀ ሕሙማንን ይፈውሳል የሚጽፍበት ብዕር ነጥቆ ከመሬት ላይ ቢያርፍ ወዲያው በቅሏል ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከአኃው ጋር ለተልእኮ ሲሄድ ከመንገድ ምሳ ለመብላት አረፍ ብለው ድርሻ ድርሻቸው ተከፍለው ሲበሉ አባ ገሪማ ቅዳሴ እንዳለ አውቆ ድርሻውን የበላ መስሎ አስቀመጠ ለአኃው ግን የበላ መስሏቸው ነበር ከተላኩበት ቦታ ሲደርሱ መሥዋዕት ተሰርቶ አንድ ቀዳሽ ጐሎባቸው ሲጨነቁ አገኙ አባ ገሪማ ገብቶ ቀደሰ ኅጽዎቹም በልቶ ቀደሰ እያሉ ያሙት ጀመር ወደ በዓታቸውም ሲመለሱ አባ ገሪማ በልቶ ቀደሰ ሕልፍቶ ለአበምኔቱ ለአባ ጰንጠሌዎን ነገሩት ።

አባ ጰንጠሌዎን አባ ገሪማን አስጠርቶ ሲመጣ ብዙ ሰዎች አብረውት መጡ ልጄን የምጠይቀው አለኝና ውጡልኝ አላቸው በዚህ ጊዜ አባ ገሪማ ምን ሰዎች ብቻ ዕንጨቶችም ድንጊያዎችም ይወገዱ እንጂ ብሎ በተናገረ ጊዜ ከሰዎች ጋር ደንጊያዎችም ዕንጨቶችም አምስት ምዕራፍ ሸሹ አባ ጰንጠሌዎንም ገረምከኒ ኦ ወልድየ ይስሐቅ አለው ከዚያ ወዲህ ገሪማ ተባለ ፡


ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ በእኔ ስም አምኖ በአንተ ቃልኪዳን በመማጸን በስምህ የተራበ ያበላውን የተጠማ ያጠጣውን የታረዘ ያለበሰውን በስምህ ቤተክርስቲያን የሠራውንና ያሠራውን በመታሰቢያህ ዕለት መባ ያቀረበውን ሁሉ ምሬልሃለሁ በማለት ተናግሮት ተሠውሯል ፡ አባ ገሪማም ፳፯ ዓመት በአርዐተ ምንኩስና ተጸምዶ ፈጣሪውን ካገለገለ በኋላ ሰኔ ፲፯ ቀን ተሠውሯል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያገለግሉ ቅዱሳን ሁሉ የሚሰጣቸው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተለያየ ነው ለአንዱ ድውይ የመፈወስ ፡ ለአንዱ አጋንንትን ከሰው የማባረር ለአንዱም ትንቢትን የመናገር ለአንዱም የማስተማር ፣ ለአንዱም ተአምራት የማድረግ ሀብት ወዘተ ይሰጣቸዋል በሁሉ አድሮ ሁሉን የሚሠራ ግን አንድ መንፈስ ቅዱስ ነው ።

ሮሜ ፲፪·፮ — ፰ ፩ኛ ቆሮ ፲፪·፰ -- ፲፩

**አባ ገሪማም ልዩ ልዩ ተአምራት እንዳደረጉና አጋንንትንም ከሰዎች ያባረሩ መሆኑ በመጽሐፈ ገድሉ ተመዝግቧል ተጋድሎውን ከፈጸሙ በኋላ ደግሞ በሕይወተ ሥጋ እንደ ሄኖክ እንደነ ኤልያስ ወዘተ..ተሠወሩ እንጂ አልሞቱም። በተሠወሩበት ሰኔ ፲፯ ቀን ስማቸውን ጠርቶ ለተራበ ያበላውን የተጠማ ያጠጣውን የታረዘ ያለበሰውን ጧፍ ገዝቶ ዕጣን ዘቢብ ቋጥሮ በስማቸው ለታነፁ አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን እንደሚምርላቸው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ተቀብለዋል።**

ስለዚህ በተጠቀሰው ዕለት ሰኔ **፲፯ ቀን መታሰቢያቸውን በማድረግ በጻድቁ ስም የተራበ በማብላት** የተጠማ በማጠጣት ከጻድቁ በረከት ለመሳተፍ እንችል ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ በቸርነቱ ይርዳን ። አሜን!!

ቀ·ሲ· ልሣኑ በዛብኅ





# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

| ተ.ቁ | ካለፈው የቀጠለ የፓትርያርኮች ስም | የተሾሙበት ዓመተ ምሀረት | በፓትርያርክነት ያገለገሉበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 79 | አባ ቴዎዶስዮስ (ሁለተኛ) | 1294 | 6 ዓመት ከ7 ወር |
| 80 | " ዮሐንስ (ስምንተኛ) | 1300 | 10 ዓመት |
| 81 | " ዮሐንስ (ዘጠነኛ) | 1320 | 6 ዓመት ከ5 ወር |
| 82 | " ቢኒያሚን (ሁለተኛ) | 1327 | 11 ዓመት ከ8 ወር |
| 83 | " ጴጥሮስ (አምስተኛ) | 1340 | 8 ዓመት ከ3 ወር |
| 84 | " ማርቆስ (አራተኛ) | 1350 | 14 ዓመት ከ5 ወር |
| 85 | " ዮሐንስ (ዐሥረኛ) | 1364 | 6 ዓመት ከ2 ወር |
| 86 | " ገብርኤል (አራተኛ) | 1370 | 8 ዓመት ከ3 ወር |
| 87 | " ማቴዎስ (አንደኛ) | 1378 | 30 ዓመት ከ5 ወር |
| 88 | " ገብርኤል (አምስተኛ) | 1409 | 19 ዓመት ከ8 ወር |
| 89 | " ዮሐንስ (ዐሥራ አንደኛ) | 1428 | 24 ዓመት ከ11 ወር |
| 90 | " ማቴዎስ (ሁለተኛ) | 1455 | 13 ዓመት |
| 91 | " ገብርኤል (ስድስተኛ) | 1466 | 8 ዓመት ከ10 ወር |
| 92 | " ሚካኤል (ስድስተኛ) | 1477 | 1 ዓመት |
| 93 | " ዮሐንስ (ዐሥራ ሁተኛ) | 1480 | 3 ዓመት ከ4 ወር |
| 94 | " ዮሐንስ (ዐሥራ ሦስተኛ) | 1483 | 40 ዓመት ከ10 ወር |
| 95 | " ገብርኤል (ሰባተኛ) | 1526 | 43 ዓመት |
| 96 | " ዮሐንስ (ዐሥራ አራተኛ) | 1573 | 15 ዓመት ከ4 ወር |
| 97 | " ገብርኤል (ስምንተኛ) | 1590 | 11 ዓመት |
| 98 | " ማርቆስ (አምስተኛ) | 1610 | 10 ዓመት |
| 99 | " ዮሐንስ (ዐሥራ አምስተኛ) | 1621 | 10 ዓመት |
| 100 | " ማቴዎስ (ሦስተኛ) | 1631 | 10 ዓመት |
| 101 | " ማርቆስ (ስድስተኛ) | 1650 | 10 ዓመት |
| 102 | " ማቴዎስ (አራተኛ) | 1660 | 14 ዓመት ከ8 ወር |
| 103 | " ዮሐንስ (ዐሥራ ስድስተኛ) | 1676 | 42 ዓመት ከ3 ወር |
| 104 | " ጴጥሮስ (ስድስተኛ) | 1718 | 7 ዓመት ከ6 ወር |
| 105 | " ዮሐንስ (ዐሥራ ሰባተኛ) | 1727 | 18 ዓመት ከ3 ወር |
| 106 | አባ ማርቆስ (ሰባተኛ) | 1797 | 13 ዓመት ከ2 ወር |
| 107 | " ጴጥሮስ (ሰባተኛ) | 1810 | 42 ዓመት ከ3 ወር |
| 108 | " ቄርሎስ (አራተኛ) | 1854 | 6 ዓመት ከ8 ወር |
| 109 | " ዲሚጥሮስ (ሁለተኛ) | 1862 | 7 ዓመት ከ7 ወር |
| 110 | " ቄርሎስ (አምስተኛ) | 1874 | 53 ዓመት ከ9 ወር |
| 111 | " ዮሐንስ (አሥራ ስምንተኛ) | 1770 | 6 ዓመት ከ7 ወር |
| 112 | " ማርቆስ (ስምንተኛ) | 1797 | 13 ዓመት ከ6 ወር |
| 113 | " ዮሐንስ (ዐሥራ ዘጠነኛ) | 1929 | 13 ዓመት ከ6 ወር |
| 114 | " ማካሪ (ሦስተኛ) | 1944 | 1 ዓመት ከ6 ወር |
| 115 | " ዮሳብ (ሁለተኛ) | 1946 | 10 ዓመት ከ5 ወር |
| 116 | " ቄርሎስ (ስድስተኛ) | 1959 | 11 ዓመት ከ10 ወር |
| 117 | " ሲኖዳ (ሦስተኛ) | 1971 | አሁን የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን በመምራት ላይ ያሉት ፓትርያርክ ናቸው። |



www.ethiopianorthodox.org

# በመስቀሉ አዳነን

አባታችን አዳም እናታችን ሔዋን ዕፀ በለስን በልተው ከገነት ወጥተው ሲባረሩ ተስፋ አልቆረጡም በፈታሔነቱ አንጻር መሐሪነቱ እንዳለ በተፈጥሯቸው ተመራምረው አውቀው ወደፈጣሪያቸው ቢያለቅሱ እግዚአብሔር አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ እንደሚያድናቸው ነገራቸው ይህም ቃል አልታጠፈም በተባለው ዘመን ክርስቶስ ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ ከአዳም እስከ ዕለተ ዓርብ የነበሩትን ነፍሳት ሁሉ ከሲኦል አወጣቸው ፡ ነፃነትንም ሰበከላቸው ፩ኛ ጴጥ ፫፡፲፰ ።

ሞትን በሞቱ ደምስሶ ከተነሣ በኋላ አልተነሣም የሚታየውም ምትሐት ነው በማለት አይሁድ ያስወሩ ስለነበሩ መነሣቱን ለማረጋገጥና ለማስረዳት ሲል ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ እየበላና እየጠጣ ፵ ቀን ቆይቶ ወደሰማይ በዓቢይ ክብር በይባቤ መላእክት ዓረገ ከዕርገቱ በኋላ የተሰቀለበት የዕንጨት መስቀል ዕውር እያበራ ለምፅ እያነፃ ሙት እያስነሣ ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስትና እምነት እንዲገቡ ያደርግ ጀመር ይህ ገቢረ ተአምራት ለክርስትና እምነት ተከታዮች አስደሳች ሲሆን በአይሁድ ላይ ከፍተኛ ፍርሃትን ፈጠረ የአይሁድ ዓላማ የክርስቶስ አዳኝነት እንዳይነገር ማንኛውም ሰው ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዳይሄድ ማገድ ነበር ነገር ግን ሕዝቡ ሌት ከቀን የክርስቶስ መስቀል ወደሚገኝበት እየገሠገሠ በመሄድ መስቀሉን በመዳሰስ ይፈወስ ስለነበር በዓዋጅም በማስፈራራትም ሊታገድ አልቻለም ።

አይሁድ ብዙ ምክክር ካደረጉ በኋላ የክርስቶስን መስቀል ሰው ከማያውቀው ቦታ ደብቆ ከማስቀመጥ በቀር ሌላ መፍትሔ አለመኖሩን ተገንዝበው ከከተማው ዳርቻ ጉድጓድ ምሰው የጌታችን መስቀል ከፈያታዊ ዘየማንና ዘፀጋም መስቀሎች ጋር ቀብረው በከተማው የሚኖረው ሕዝብ ሁሉ ጥራጊውን እየወሰደ መስቀሉ ከተቀበረበት ጉድጓድ ላይ እንዲደፋ ታዘዘ በትእዛዙ መሠረት በከተማ የሚኖረው ሁሉ ቆሻሻውን ያፈስበት ጀመር ከውስጡ የክርስቶስ መስቀል መቀበሩን የሚያውቁት ግን አይሁድ ብቻ ነበሩ ።

ይህ ቦታ ለብዙ ዘመናት የቆሻሻ መድፊያ ሆኖ ኑሯል ከጊዜ በኋላ ቦታው እንደ ተራራ ሆኖ ለመታየት በቅቷል ። ከ፪፻፶ ዓመት በኋላ የቆስጠንጢኖስ እናት ዕሌኒ ተነሣች የክርስቶስ መስቀል ጎልጎታ በተባለው ቦታ ተቀብሯል የሚል ዜና ስለሰማች ቆፍራ አውጥታ ቤተ መቅደስ አሠርታ በክብር ለማስቀመጥ አስባ ለልጇ ለቆስጠንጢኖስ ነገረችው እርሱም የእናቱን ሐሳብ ተቀብሎ ብዙ ሠራዊት ጨምሮ ሰደዳት ዕሌኒም ወደኢየሩሳሌም ሂዳ መስቀሉ ያለበትን ብትጠይቅ ዜናውን የሚነግራት አጣች ከብዙ ምርመራ በኋላ ኪርያኮስ የሚባል አንድ ሽማግሌ ቦታውን ለይቼ አላውቀውም እንጂ በዚያ አቅጣጫ ይመስለኛል ብሎ ወደ ጎልጎታ ኮረብታ አመለከታት ።

ቦታውን ለይቶ አውቆ ለማስቆፈር ይቻል ዘንድ ንግሥት እሌኒ ሁሉም ሰው እንጨት እየያዘ መጥቶ ደመራ እንዲደምር አደረገችና በእሳት እንዲቃጠል አዘዘች ደመራው ተቃጥሎ ፍሕም ሲሆን ሦስት ጊዜ ዕጣን አስመጥታ በፍሕሙ ላይ እንዲያደርጉት አዝዛ ቢያደርጉት የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ተመልሶ እንደቀስተ ደመና ከምድር ላይ ተተክለ ያንን ምልክት በማድረግ ዕሌኒ ቁፋሮው ከዚያው ላይ እንዲጀመር አዝዛ መስከረም ፲፯ ቀን ተጀምሮ መጋቢት ፲ ቀን የጌታችን መስቀል ተገኝቷል ።

በቁፋሮ ያተገኙት መስቀሎች ሦስት ስለነበሩ ከመካከላቸው የክርስቶስን መስቀል ለይቶ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆነ ነገር ግን እያንዳንዱን እየወሰዱ በሞተ ሰው ሬሳ ላይ አስቀመጧቸው የፈታዊ ዘየማንም ሆነ የፈያታዊ ዘፀጋም መስቀሎች ምንም ያሳዩት ምልክት አልነበረም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ግን የሞተውን ሰው አስነሥቶ እንዲናገር አድርጓል ። ድውይ ፈውሷል ዕውር አብርቷል ለምፅ አንጽቷል ከዚያ በኋላ ዕሌኒ ንግሥት ቤተ ክርስቲያን አሠርታ በክብር አስቀምጣዋለች ይህ የመታሰቢያ በዓል በየዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን ደመራ ተደምሮ ፲፯ ቀን ተቃጥሎ በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል መታሰቢያነቱ የመስቀል ቢሆንም ምክንያቱ ግን መስከረም ፲፯ ቀን ዕሌኒ ቤተ ክርስቲያን አሠርታ መስቀሉን ያስገባችበት ሲሆን መስከረም ፲፯ ቀን ደግሞ የጌታችን መስቀል ለማግኘት ቁፋሮ ያስጀመረችበት ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው" ብሎ እንደተናገረው ክርስቶስ በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ሠውቶ ደሙን አፍስሶ እንዳዳነን እናምናለን ።

በመስቀሉ እንዳዳነንም ለመግለጽ በአንገታችን መስቀል እናስራለን በባሕላችን መሠረት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ቀሳውስት በእጃቸው መስቀል ይዘው ይባርካሉ ይቀድሳሉ ።

መስቀልን በአንገት ማሠርና በእጅ መጨበጥ ብቻ ከስሕተትና ከበደል ከኃጢአትና ከተንኮል ሊያድን አይችልም በሐሳባችንም እንደክርስቶስ መስቀል ይኖርብናል በክርስቶስ መስቀል መዳናችን የምናምን ሁሉ ስለ እኛ የተሰቀለውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለአንዳፍታ እንኳን መዘንጋት አይኖርብንም እርሱ ስለእኛ ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሏል ስለእኛ ተገርፏል ። ስለ እኛ በፍርድ አደባባይ ቆሞ በሐሰት ተፈርዶበታል ። ስለእኛ መራራ ሐሞትን ተጎንጭቷል ስለእኛ ተሰድቧል ተዋርዷል ተንቋል ።

በእርሱ ሞት እኛ ሕይወትን አግኝተናል በእርሱ ውርደት እኛ ከብረናል ስለእርሱ ስንመሰክር የምንቀበለው መከራ ሁሉ ዋጋን የሚያስጠን ስለሆነ መሰቀቅና መመረር አይኖርብንም በመስቀሉ ያዳነን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመከራ እንምሰለው በመከራ ከመሰልነው በክብርም ለመምሰል እንችላለንና ።

የመስቀልንም መታሰቢያ በዓል ስናከብር ሁለት ነገሮችን አተኩረን እንድንመለከት ያሳስበናል አንደኛ የወርኃ ክረምት ማለቂያ የተቃረበበት በመሆኑ የአበባዎችን መፍካት የውሃዎችን ጥራት የዝናማትን ትዕግሥት ስንመለከት ወኩሎ በጥበብ ገበርከ ሁሉን በጥበብ አከናውነህ ፈጠርህ ብለን እንድናደንቅ ሲያስገድደን ።

የደመናትን ከጠፈረ ሰማይ ላይ መገፈፍ የፀሐይን ጨረርና ሙቀት ስንመለከት ደግሞ ከፍ ያለ ደስታ እየተሰማን በዓሉን በደስታ ለማክበር እንችላለን እንግዲህ በመስቀሉ ከዲያብሎስ ተገዥነት ከኃጢአት ባርነት ያዳነን አምላክ ወደፊትም ከዲያብሎስ ተገዥነት ነፃ ሆነን እንድንኖር በሐጹረ መስቀሉ ይጠብቀን ።

አሜን

ቀሲስ ጎልሣኑ በዛብኅ

ማሳሰቢያ፦

እነዚህ ሁሉ የተሾሙት በየጊዜው ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩት ፓትርያርኮች ምትክ እየተመረጡ ነበር ። አልፎ አልፎም ምርጫዎች በተለያዩ ምክንያቶች በዘገዩ ቁጥር መንበረ ፓትርያርኩ በተጠባባቂ አባቶች ሲመራ የቆየባቸው ጊዜዎች ነበሩ ።

ከዚህ በላይ የተጻፈውን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ስም ዝርዝር ያገኘሁት የኮፕቶች ታሪክ በሚል ርእስ በኤሪስ ሀቢብ ኤል ማስሪ በ1978 ዓ/ም በእንግሊዝኛ ከተጻፈው መጽሐፍ ከገጽ 563–566 ነው ።

የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጠር ብሎ ለሦስት ዓመት ያህል በተከታታይ በትንሣኤ መጽሔት ታትሞ በመውጣት ስለተጠናቀቀ ፤ ለወደፊት የሦርያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይቀጥላል ።

ሉሌ መልአኩ

# ካልተረዳዱ ኑሮ ከባድ ነው

"ሐምሳ ሎሚ ላንድ ሰው ሸክሙ ነው ለሃምሳው ሰው ጌጥ ነው" እንደሚባለው ሁሉ ኑሮንም ላንድ ሰው ብቻ ቢያሸክሙት ሸክሙ ይከብደዋል ፤ ተከፋፍሎ ቢሸከሙት ግን ስለሚቀል ኑሮ ጣእምና በረከት ያለው ይሆናል ።

ይህንንም ያወቀው አምላካችን እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው "ገነትን ጠብቃት ተንከባከባት" እንዳለው እናገኛለን ። ይህም ብቻውን ሳይሆን ከረዳቱ ጋር እየተረዳዳ ይሥራ ማለት እንደሆነ ምሥጢሩ አይሰወርብንም ቀጥሎም ሥራ ጠቃሚ መሆኑን ሲያስተምረው ጥረህ ግረህ በላብህ እንጀራህን ብላ ብሎታል ።

እርሱም ከረዳቱ ጋር ትእዛዙን ተቀብሎ በመሥራት ኑሮውን አሻሿል ። በየጊዜው የተነሳውም ትውልድ የርሱን አርአያ በመከተልና በመሥራት ላይ ይገኛል ። በመሆኑም በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰልፈው ግዴታቸውን በመወጣት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ያስተዳድራሉ ። ይህንንም





www.ethiopianorthodox.org

ሲፈጽሙ በትዳር ዓለም ወይም ከወላጆች ጋር በመኖር ነው ።

በጋብቻ ዓለምም ላይ ሆነው ፍጹም የሆነ የቤተሰብ ፍቅር ሲያድርባቸውና የቤተሰባቸው ምሰሶ ማለት ቋሚ አስተዳዳሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል ። ለዚህም የትዳር ጓደኞቸው ምክርና ሐሳብ መለየት የለበትም ። ይህ ካልሆነ ግን ኑሮአቸው በተስተካከለና በተሟላ አቋም አይካሔድም ።

ስለዚህ ተከባብረውና ተሳስበው መኖር ይፈለግባቸዋል ። በመሆኑም ባልና ሚስት ተናንቀው ሣይሆን ተከባበረው መኖር እንደሚገባቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን ምሳሌ አድርጎ አቅርቧል ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀደሳት ስለርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷልና ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደራሳቸው አድርገው ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባል ። ሚስቱንም የሚወድ ራሱን ይወዳልና ማንም ራሱን የሚጠላ ከቶ የለም። ስለዚህም እያንዳንዱ የገዛ ሚሽቱን እንደራሱ አድርጎ ይውደዳት”ብሏል ኤፌ·፭—፳፮—፴፫።

ይህንን የጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለምን ሆን ለእኛ ለምዕመናንና ለምእመናት ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠልን እናውቃለን ፍጡሮቹንም እንደራሱ አድርጎ ስለወደደን ፍቅሩን በመስቀል ላይ ገልጦልናል ። ቀቀሎ ደግሞ በጋብቻ ክቡርነት ላይ ያሉት የባልና የሚስትም ፍቅር የተሟላ መሆን እንዳለበት ያስረዳል ።

ስለዚህ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ይህን በመሰለ በመረዳዳት እየኖሩ የቤተሰብ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው እንጂ የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈለጉ ወንዶችም ሚስቶቻቸውን ባረጁ ጊዜ ወደ ሌላይቱ ተመልክተው ማመንዘር እንደማይገባቸው ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል ፤

“ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ እንደተወደደችም ዋልያ እንደተዋበችም ሚዳቋ በጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ በፍቅርዋም ሁል ጊዜ ጥገብ እንጂ ስለምን ጋለሞታ ሴት ትወዳለህ ። የሌላይቱንስ ብብት ታቅፋለህ” ይላል ። ምሳሌ ፭፥ ፲፰ —፳

እንዳለውም ይህን የመሰለውን መልካም ዓላማ ትቶ ከሳች ፤ ጠቆረች ፤ ታመመች ፤ ሰነፈች ፤ በሚል አጉል አስተሳሰብ ተነስቶ የራስን አበባ በመተው ሌላይቱን ውበት ያላትን ፤ ሀብት ወገንና ዘመድ ያላትን መፈለግ ሕገ ወጥነት ከመሆኑም ሌላ የቤተሰብን ፍቅር የሚበክልና ትክክለኛ ያልሆነ ድርጊት በመሆኑ የትዳር እንቅፋት ስለሆነ ይህን ተገንዝቦ የልጅነት ሚስትን አክብሮ መያዝ ተገቢ ነው ።

በተጨማሪ ጠቢቡ ሰሎሞን ይህን ያለበት አንድ ምክንያት አለው ወንዱ በወጣትነቷ ጊዜ የአበባዋ ወራት ደምቆ ሁሉን በሚስብበት እና በሚማርክበት ሁሉም ላግባሽ እያለ በሚጠይቅበት የወጣትነት ዘመን አጭቶ ያገባሃትን ሚስት እንደ መጀመሪያው ወቅት ውደዳት ውበቷም መልኳም እንደ ጽጌረዳ አበባ መስላ ትታይህ እንጂ በሁለታችሁ መካከል ለውጥ አይኑር እሷም ብትሆን እንዲሁ ትመልከተው ማለቱ እንደሆነ ሊቃውንት አስተያየት ይሰጡበታል ።

እንግዲህ ሴቶች የሆኑ ሁሉ የጌጥ አይነት የልብስ ሞድ በየጊዜው መለዋወጥ ፤ በገበያ ያዩትን ሁሉ ገዝቶ መምጣት ሲበዛ ያሰለቻል ። ለሴቶች የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር ኑሮ እንዳይሰለቻቸው ከሥራቸው መልስ የጓሮ አትክልትን መትከል ፤ በቤት አካባቢ አበባን ተክሎ ውኃ እያጠጡ እንዲያድግ መንከባከብ ፤ መጽሐፍ ማንበብና በማኅበራዊ ኑሮ በኩልም እየተገኙ ታሳታፊ መሆን ፤ ሥራንም ሠርቶ ከጨረሱ በኋላ የሥራ ልብስን ለውጦ አምሮና ተውቦ ባል ከሥራ ሲመጣ በፈገግታ ተቀብሎ በፈገግታ መሸኘት በበዓል ቀን ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የጸሎቱና የቅዳሴው ተካፋይ ከሆኑ በኋላ ቅዱስ ቃሉን ሰምቶ ወደቤት መመለስ ኑሮን እንዳይሰለች ከማድረጉም በላይ ከረዳት ጋር ያፈቃቅራል ያስተባብራል ።

ስለዚህ ኑሮ የማይሰለችና የጣፈጠ እንዲሆን መተሳሰብ መከባበር ያስፈልጋል ።

ወ/ት መዓዛ አስማማው



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስተምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቍ·
የመልእክት ሣ·ቍ· 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org